# የብሉይ ኪዳን ታሪክ

# መቅድም

የብሉይ ኪዳን ታሪክ የተሰኘው መጽሐፍ የብሉይ ኪዳንን ይዘት በአጭሩ የሚያቀርብ ነው። መጽሐፉ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ በሙሉ ለማቅረብ ስለሚፈልግ ለእያንዳንዱ ሁኔታ ማብራሪያ ለመስጠት አይችልም፤ ተማሪ ትምህርቱን ሲከታተል ይህንን ማብራሪያ በሌላ የትምህርት ወቅቶች ያገኘዋል። በመሆኑም መምህር ሲያስተምር ታሪኩን በሙሉ መሸፈን ስለሚያስፈልገው በሚያውቅና በሚወድ ታሪኮች ላይ ብዙ ሰዓቶች እንዳያጠፉ መጠንቀቅ ያሻዋል። ይህ የመጀመሪያ እትም ስለሆነ አንዳንድ የፊደልና የአቀራረብ ጉድለቶች ሊገኙ ይችላሉ፤ ወደ ፊትም ሰፋ ባለ ሁኔታ ታሪኩን ለማጠናቀር ስላቀድን በሁለተኛው እትም የበለጠ እንደምትደሰቱ እንተማመናለን።

ጥቅምት 1985 ዓ.ም.

## ማውጫ

ገጽ


1. መግቢያ .................................... 4
2. ከፍጥረት እስከ ባቢሎን ግንብ .................... 5
3. የመጀመሪያው የዓለም መንግሥት .................... 10
4. ጥበዕ .................................... 13
5. ከአብርሃም እስከ ሙሴ .......................... 14
6. የእስራኤል ጉረቤቶች .......................... 20
7. የአሦር መንግሥት ............................ 24
8. የእስራኤል መንግሥት .......................... 26
9. የይሁዳ መንግሥት ............................ 30
10. የአሦራውያን አስተዳደር ...................... 36
11. የባቢሎናውያን አስተዳደር .................... 38
12. የፋርስ አሸናፊነት .......................... 41
13. የይሁድ ወደ ከነዓን መመለስ .................... 42
14. መጽሐፈ አስቴር ............................ 43
15. የምኩራብ አምልኮ አጀማመር .................... 45
16. በኪዳናት መካከል .......................... 45


# የብሉይ ኪዳን ታሪክ

## መግቢያ

የብሉይ ኪዳን ታሪክ የሚተርከው ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠርና አኗኗር ነው፤ ታሪኩም የሚጀምረው ምድር ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ይኸውም በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ላይ ይገኛል። በዘፍጥረት 1፡16 ላይ የተጠቀሱት ብርሃናት ከተፈጠሩ ብዙ ሚሊዮን ዓመታት ያለፏቸው ቢሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ ሰማይና ምድር የተፈጠሩበትን ቀን በውል አያስረዳም። ሆኖም እግዚአብሔር ምድርና ሰማይን መፍጠሩን ሰዎች እንዲያውቁ በአጠቃላይ አገላለጽ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» ተብሎ ተመዝግቦአል።

የብሉይ ኪዳን ታሪክ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው። የሰው ልጅ በሙሉ ሊመለክ የሚገባውን ፈጣሪውን ትቶ ጣዖትን በማምለክ ከእግዚአብሔር ራቀ። በሰማይም ሆነ በምድር አንድ አምላክ ብቻ እንዳለና እርሱንም ብቻ ማምለክ እንደሚገባን እንዲያስተምሩ አብርሃም ከተባለ ሰው ዘር የመጡትን እስራኤላውያንን መረጠ። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር በሥጋ ከይሁዳ ወገን የተወለደውን ክርስቶስን እስነሥቶ መድኃኒትና ቤዛ አድርጎ ለዓለም ሁሉ ሰጠው።

እግዚአብሔርም ለዚህ ዕቅዱ ሦስት አቢይ እርምጃዎችን ወሰደ። ይኸውም፡-

1. ዓለም ሁሉ በዘራቸው በኩል እንዲባረክ እግዚአብሔር የእስራኤልን ነገድ መረጠ።
2. ይህም ዘር ከዳዊት ቤት ተነሥቶ አይሁድንና አሕዛብን ሁሉ ይባርካል።
3. ይህም ከዳዊት ቤተሰብ የሚነሣው ዘር ክርስቶስ ኢየሱስ ሲሆን እግዚአብሔር አብም የማዳን ዓላማውን ለመፈጸም ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮታል።

# የብሉይ ኪዳን ታሪክ

## ምዕራፍ አንድ

## ከፍጥረት እስከ ባቢሎን ግዞት

### ክፍል 1

ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ወድቀው ከእግዚአብሔር እስከተለዩበት ቀን ድረስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ሆኖ ይሠራ ነበር። እርሱ ራሱም እግዚአብሔር ነበረ፤ ዮሐ.1፡1። የተፈጠረው ነገር ሁሉ ለክርስቶስ ክብር እንዲኖር እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ለሰው ልጅ ጥቅምና መኖርያ እንዲሆኑ በልጁና ለልጁ ፈጥሮአል፤ ዕብ.1፡2፤ ቆላ.1፡16፤ ኤፌ.3፡9፤ ራዕይ 4፡11፤ ኢሳ.45፡18። እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ልጁ እንደ ነበረ በምሳሌ 8፡22-33 እንመለከታለን።

### እግዚአብሔር ምድርን ለሰው መኖርያ እንዲሆን አዘጋጀ

ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ

1ኛ ቀን ብርሃን፡- ቁ.1 እና 2
2ኛ ቀን ጠፈር፡- ቁ.6-8
3ኛ ቀን ሣር፣ ቡቃያና ዛፍ፡- ቁ.9-13
4ኛ ቀን ፀሐይ፣ ጨረቃ ከዋክብት፡- ቁ.14-19።
5ኛ ቀን ወፎችና ዓሦች፡- ቁ.20-23
6ኛ ቀን እንስሳት፣ አራዊትና ሰው፡- ቁ.24-31
7ኛ ቀን ቀደሰው ባረከውም፡- ምዕ. 2፡1-3

### ተድላ በኤደን ገነት ዘፍ.2፡8-19

ሰው ከመፈጠሩ አስቀድሞ እግዚአብሔር አትክልትን፣ እህልንና ፍራፍሬን ከዚያም ከጥፋት ውኃ በኋላ ማለት ኖኅ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ሥጋን እንዲበላ ለሰው ልጅ እንስሳትን አዘጋጅቶለታል፤ ዘፍ.2፡8-19፤ ዘፍ. 1፡29-30፤ 2፡9፤16፤ 9፡3፤30፤ ኢሳ.11፡6-9።



### ገነት የምትገኝበት ሥፍራ

በዘፍጥረት ምዕራፍ 2፡8 እና 14 መሠረት ገነት ከኤደን ምሥራቅ ማለት ከኢትዮጵያ አቅራቢያ ከምትገኘው የዓረብ ግዛት በሆነችው በሶርያ ምድር ውስጥ እንደምትገኝ እንመለከታለን። ልዩ ሥፍራውም ምናልባት በሁለቱ ወንዞች ማለት በኤፍራጥስና በጤግሮስ መካከል ሳይሆን አይቀርም። የጥንቱ የወንዞቹ መንገድና የምድሩ የካርታ አቀማመጥ ከአሁን ጋር በጣም ይለያያል። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጊዜ በኤደን ገነት ውስጥ ከሰጠው አዝርዕትና ፍራፍሬ ዛሬ የምናያቸውን የተለያዩ ዕፀዋቶች ተራብተው እናገኛቸዋለን።

<u>የሰው አፈጣጠር</u> እግዚአብሔር ሰውን ከመሬት ትብያ አንሥቶ በራሱ መልክና ምሳሌነት ፈጥሮታል፤ ዘፍጥ.2፡7፤ 21-22። እርሱም ሕያው ነፍስ ያለው ፍጥረት መሆን የጀመረው እግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስን እፍ ባለበት ጊዜ ነበር፤ ዘፍ.2፡17። ሰውም በወቅቱ እንዲነጋገርበት እግዚአብሔር የሰጠው ቋንቋ ነበረው፤ ዘፍ.2፡19-29፤ በዚያን ጊዜም አዳም የተባለው የመጀመሪያው ሰው ዋነኛ ሥራ እንዲኖርባት የተሰጠችውን ገነትን መጠበቅ በውስጥዋም ያሉትን ፍጥረቶች ሁሉ መግዛት ነበር፤ ዘፍ.1፡28፤ 2፡15።

### የሰው በኃጢአት መውደቅ

የመጀመሪያው ሰው አዳም ረዳት እንድትሆነው ከተሰጠችው ከሔዋን ጋር በኤደን ገነት ሲኖር ሳለ የራሱን ፍጹም ምርጫ ከማድረግ መብት ጋር ከቱና ደግ ከምታስታውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ አዘዘው። እርሱም በተሰጠው መብት መሠረት ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ የእግዚአብሔር ጠላትና ተቀናቃኝ ለሆነው ለሰይጣን መታዘዝን መረጠ። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር እርግማን ኃጢአተኛ በሆነው የሰው ዘር ሁሉ ላይ ደረሰ፤ ሮሜ 8፡22።

እግዚአብሔር እባብን አፈር እንድትበላና በሆድዋ እንድትሄድ ረግሟታል፤ ዘፍ.3፡14-15።

- ሔዋን ደግሞ በምትወልድበት ጊዜ ጣርዋ እንዲበዛና የመንፈስና የሥጋ ሞት እንድትሞት ፈርዶባታል፤ ዘፍ.3፡16፤19።
- አዳም ደግሞ በወዙ ጥሮ ግሮ እንዲበላ መሬት ስለ እርሱ እሾህና አሜከላ እንድታበቅልና እርሱም በሔዋን ላይ የተፈረደባትን ሁለቱን ዓይነት ሞት እንዲሞት ተበይኖበታል፤ ዘፍ.3፡19።
- መሬትም እሾህና አሜከላ እንድታበቅል ተረገመች፤ ዘፍ.3፡17።

ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር የምትገለባበጥ ሰይፍና የመልአክ ዘበኛ በገነት በር ላይ አቁሞ ሰውን ከገነት አስወጥቶ ወደ ውጭ አባርታል። ሆኖም እግዚአብሔር ለዘለዓለም የማይቆጣና የማይቀበፍ ምሕረቱ የበዛ አምላክ በስሆን የመዳንን ተስፋ በክርስቶስ በኩል ለመስጠት ቃል ኪዳን አደረገ፤ ዘፍ.3፡23-24፤ 3፡15።

# ክፍል 2

እንደ ዕብራውያን ዘመን አቆጣጠር አዳም በኃጢአት ከወደቀበት አንሥቶ እስከ ጥፋት ውኃ ድረስ ያለው ዘመን ረዘም ያለ ነው። የመጀመሪያዎቹ በተከታታይ የተወለዱት የአዳም ልጆች አቤልና ቃየል ይባላሉ፤ ዘፍ.4፡1-2። አዳምም እርሱንና ልጆቹን ከእግዚአብሔር በለየው ኃጢአት ምክንያት ራሱ፥ አቤልና ቃየል የየራሳቸውን መሥዋዕት አደረጉ። አቤልም የደምን መሥዋዕት አደረገ። ቃየል ግን ይህን ባለማድረጉ መሥዋዕቱ ሊሰማለት አልቻለም። በአዲስ ኪዳን እንደምንረዳው የአቤል መሥዋዕት የክርስቶስን ቤዛነት የሚገልጽ ሆኖ እናገኘዋለን። የቃየል መሥዋዕት ግን ትክክል እንዳልሆነ የሚከተሉት ጥቅሶች ያመለክታሉ፤ ዘፍ.4፡2-5፤ ዕብ.11፡4፤ 1ኛ ዮሐ.3፡12። ስለዚህም ቃየል በቅንዓት መንፈስ ተነሣሥቶ እግዚአብሔር እየመከረውና እያስጠነቀቀው ላለ እምቢ ብሎ ወንድሙን ገደለው፤ ዘፍ.4፡4-7። ከዚህም የተነሣ ቃየል በዓለም ውስጥ የመጀመሪያው ነፍስ ገዳይ ስለሆነ እግዚአብሔር እርግማንን ሁሉ አፍስሶበታል፤ ዘፍ.4፡9-15። ከዚህ በኋላም ቃየል በኃጢአቱ በመቀጠል ቀማኛና አመፀኛ በመሆን ከጌታ ራቀ እንጂ ንስሐ ስላልገባ ዘሮቹ እንኳ ከእግዚአብሔር ርቀው የጠፉ ሆነዋል፤ ዘፍ.4፡16፤ 4፡23፤ 6፡5።

እግዚአብሔርም በሞተው ልጁ ምትክ ሦስተኛ ልጅ ሴትን ሰጠው። ይህም ሰው ለእግዚአብሔር የተባረከ ስለነበረ ከዘሮቹ አብዛኛዎቹ የእግዚአብሔር መልዕክተኞችና አገልጋዮች ሆኑ፤ ከእነርሱም መካከል ሄኖክና ኖኅ ይገኙባቸዋል። የሴት ልጆች የስም ዝርዝር በዘፍጥረት 5 ላይ ተመዝግቦአል።

ከማንኛውም ነገር ይልቅ ኃጢአት በሰዎች ልጆች ዘንድ እንዲበዛ ያደረገው አማኞች ማለት በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት እንደ ሥጋቸው ፈቃድ የሚኖሩትንና ጣዖትን ከሚያመልኩት ሰዎች ጋር መጋባታቸውና እግዚአብሔር በማይወደው በከፋት ኑሮ ውስጥ መግባታቸው ነው፤ ዘፍ.6፡1-2። አማኞች ያላመኑትን ማግባታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተከለከለ ከመሆኑም በላይ ይህን ሕግ በመተላለፍ አማኝ የሆነ ሰው ከዓለማዊ ጋር ቢጋባ የኖኅ ልጆች ፍርድ ይደርስበታል፤ 2ኛ ቆሮ.6፡14-18። ፍርድ እንዲመጣበት የሚያደርገውም ካላመነው ጋር በኃጢአቱ ተባባሪ መሆኑ ነው፤ ራዕይ 18፡4።

ሰዎች ሁሉ የክርስቶስን ትዕዛዝ የሰሙ ቢሆንም እንኳ በሥጋ ወገናቸው ሆኖ ወደ እነርሱ የመጣውን ክርስቶስን አልተቀበሉትም። የጥንት ሰዎች እድሜ በጣም ረጅም ስለነበር የኖኅ አባት አዳም ከመሞቱ በፊት 256 ዓመት ኖሮ ነበር። ስለዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን ቃል ከአዳም፥ ከሴት፥ ከሄኖክና እንደዚሁም ከቀሩት ሁሉ ስምታለች የሚለው ታሪክ እርግጥ ነው።

ሄኖክ ኃጢአተኞችን እንዲወቅስና ስለ ክርስቶስ መምጣት ከቀሩት አእላፋት ቅዱሳን ጋር ለሰብከት አገልግሎት መጠራቱን በቃሉ እናነባለን፤ ይሁዳ ቁ. 14-15፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡5። ሆኖም የሰው ልጅ በእምቢተኝነቱ እስከ መጨረሻ ድረስ ከቀጠለ የእግዚአብሔር መንፈስ እስከ ፍጻሜ ድረስ ከሰው ጋር አይኖርም፤ ዘፍ.6፡3። ኖኅም በበኩሉ የጽድቅን የምስራች በዘመኑ ለብዙዎች ያበሰረ ሰው ቢሆንም እስከዚያን ዘመን ድረስ የእግዚአብሔርን የደኅንነት ቃል ለመቀበል የተዘጋጁ ብዙም አልነበሩም።



የቃየል ዝርያዎችም በሚኖሩበት አካባቢ ከተማዎችን በመከተም፥ የሙዚቃ መሣሪያዎችን፥ ከብረትና ከናስ የተሠሩ የተለያዩ እርሻና የጦር እቃዎችን በመሥራት እጅግ አዋቂዎችና ባለሞያዎች ሆኑ፤ ዘፍ.4፡7፤ 21-22።

አዳም የወለዳቸው ልጆች እጅግ ብዙ ስለነበሩ ሁሉም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ ውስጥ አልተመዘገቡም። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔርን የተከተሉትና በትዕዛዙ የሚኖሩት ከሴት ዝርያዎች ጋር አማኞች ወይም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ተጠሩ። ዓለምንና የሥጋን ፈቃድ ተከትለው ከእግዚአብሔር የተለዩት ደግሞ ከቃየል ዝርያዎች ጋር ይቆጠሩ ነበር፤ ዘፍ.5፡4።

## በዚያን ዘመን የነበሩት ሰዎች በጥፋት ውኃ አለቁ

ምክንያቱም፡-

1. የሰው ልጆች ክፋት በምድር እየበዛ ሄደ፤ ዘፍ.6፡5።
2. ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚያሰሙትን ነቢያትንና ካህናትን ከማዳመጥ ጆሮአቸውን መለሱ።
3. መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ውስጥ ለሚያደርገው የኃጢአት ወቀሳ አልተበገሩም፤ ዘፍ.6፡3።

## እግዚአብሔር የማይታዘዙትን ለማጥፋት ወሰነ

በዚያን ዘመን የሰው ልጆች በሙሉ መንገዳቸውን ከእግዚአብሔር በመመለሳቸው ፍርድን በራሳቸው ላይ አደረጉ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የጥፋትን ውኃ አመጣባቸው።

## እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን አዳነ

ኖኅና ቤተሰቡ እንዲሁም ጥቂት የዱር አራዊትና የቤት እንስሳት ለዘር እንዲተርፉ እግዚአብሔር ኖኅን መርከብ እንዲሠራ አዘዘው። እርሱም መርከቡን ሠርቶ ካበቃ በኋላ ልክ እግዚአብሔር እንደነገረው ከሚበሉት ዓይነት እንስሳት በየወገናቸውና በየጾታቸው ሰባት ሰባት ጥንድ እንዲሁም ከማይበሉት ሁለት ጥንድ እያደረገ ወደ መርከቡ አስገባ፤ ዘፍ.7፡2-3፤ 9፡6፤ 18። ኖኅና ቤተሰቡ ከላይ ከተጠቀሱት እንስሳትና አራዊቶች ጋር ወደ መርከብ ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር የመርከቡን በር ዘጋው፤ ዘፍ.7፡16። በዚያን ዘመን የነበሩ የሰው ልጆች የምሕረት ዘመን ስላበቃ በሩ ከተዘጋ በኋላ ማንም ወደ መርከቡ ሊገባ አልቻለም። ተራሮች ሁሉ እስኪከደኑ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ዘነበ፤ ዘፍ.7፡10- 8፡14። ከዚያም ዝናቡ ካቆመበት ቀን አንስቶ በመጉደል መርከቡ የአራራትን ተራራ እስከነካበት ጊዜ ድረስ የሁለት ወር ጊዜ ፈጅቶበታል። ከዚህ በኋላም ውሃው ሁሉ ደርቆ መሬቱ እስከተገለጸበት ቀን ድረስ ሌላ ብዙ ወራቶች ፈጅቶአል። በጠቅላላው ኖኅና ቤተሰቦቹ እንዲሁም አራዊትና የቤት እንስሳዎቹ የምድርን ዓይን ሳያዩ በመርከብ ውስጥ ተዘግተው የቆዩበት ጊዜ አንድ ዓመት ከ17 ቀን ነበረ።

ኖኅም ከመርከብ እንደወረደ መሠዊያ ሠርቶ መሥዋዕቱን ለእግዚአብሔር አቀረበ። ኖኅ የደም መሥዋዕትን ማቅረቡ ክርስቶስ ወደ ፊት ወደ ዓለም መጥቶ ለኃጢአት ስርየት

መሥዋዕት እንደሚሆን ማመኑን ያሳያል። እግዚአብሔርም ኖኅ ስለነበረው እምነትና ስላቀረበው መሥዋዕት ደስ አለው፤ ዘፍ.8፡20-22።

እግዚአብሔር አዳምን የሰው ዘር ሁሉ አባትና የምድር ሁሉ ገዢ እንዳደረገው ሁሉ ኖኅንም የሰው ዘር አባትና የምድር ሁሉ ገዢ አድርጎታል፤ ዘፍ.9፡1፤28።

እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ማለት ቃየል አቤልን ከገደለበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር በነፍሰ ገዳዮች ሁሉ ላይ ሞት እንዲሆንባቸው አዘዘ።

እግዚአብሔርም ሁለተኛ የሰው ልጅን በኖኅ ዘመን እንዳደረገው በውኃ እስጥም እንደማይፈጅ የቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን ቀስተ ደመናን በሰማይ ላይ ዘረጋ፤ ዘፍ.9፡8-17። ነገር ግን ዓለም በውኃ ባይሆንም ወደ ፊት በእሳት ትጠፋለች፤ 2ኛ ጴጥ.3፡10። እግዚአብሔር ሰዎች እንስሳዎችን አርደው ሥጋ እንዲበሉ የፈቀደላቸው ከጥፋት ውኃ በኋላ ነው፤ ዘፍ.9፡3-4።

በጥፋት ውኃ ጊዜ የኖኅ መርከብ አቅጣጫውን ይዞ የተጓዘው ወደ ሰሜን ስለነበረ ውኃው ከጎደለ በኋላም መርከቡ ያረፈው በሰሜን በሚገኘው ምድር ነበረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኖኅና ቤተሰቡ በወቅቱ በጣም ለምና ሀብታም ወደነበረው በደቡባዊ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ወደ ባቢሎን ምድር ተጉዘው

በዚያ ይኖሩ ጀምር፤ ዘፍጥ. 2፡10-14። እነርሱም እግዚአብሔር እንደሚፈልግባቸው በፊታቸው ተዘርግታ ባለችው ምድር ሁሉ ተሰራጭተው በመኖር ፋንታ በዚህች ለም ምድር ለመኖር ወሰኑ። በዚያም ስማቸው የሚጠራበትን ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ሠሩ። እግዚአብሔር ግን ቋንቋቸውን ሁሉ ለዋውጦ ከዚያች ምድርም በበተናቸው ጊዜ በባቢሎን ምድር አንድ ጐሣ ብቻ እንዲኖር አድርጓል። እነዚህም ጐሣዎች የሴም ዘሮች ነበሩ። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለራሱ አገልግሎት ሰጭ ሊሆን ያለውን የእስራኤልን ነገድ በዚህ ስፍራ ለይቶ ለማስቀመጥ አቅዶ ስለነበር በዚህ ስፍራ ከቤም ነገድ እንዲወለድ አድርጓል። የእስራኤል ሕዝብ ከሴም ነገድ ከተወለደ በኋላ እግዚአብሔር ከሜዲትራንያን ባሕር እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ከዚያም እስከ ፋርስ ባሕረ ሰላጤ ድረስ ያለውን ምድር ሁሉ ርስት አድርጎ ሊሰጣቸው ተስፋ ገብቶላቸዋል፤ ዘፀ.23፡31። እስካሁን ድረስ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ተስፋ የገባላቸውን ምድር ሁሉ አጠቃለው ባይዙም ክርስቶስ የሺህ ዓመቱን መንግሥቱን ሊያቋቁም በሚመጣበት ጊዜ ሁሉንም አጠቃለው እንደሚይዙ ተነግሯል።

## የሱሜሪያ ከተማ መንግሥት

ከጥፋት ውኃ በፊት የነበረው ሕዝብና ከዚያም በኋላ ሰዎች በምድር እስከተበተኑበት ጊዜ ድረስ የነበረው ሕዝብ ሱሜሪያኖች ይባሉ ነበር። እነዚህም ወገኖች ሁሉ ይናገሩበት የነበረውም ቋንቋ አንድ ብቻ ነበረ።

ስለእነዚህም ሰዎች ለማወቅ የፍርስራሽ ጥናት መርማሪዎችም ባደረጉት ሙከራ ከአንዳንድ የሸክላና የብረት ዕቃዎች፥ የጦር መሣሪያዎች፥ የሰውና የቦታ ስም የተቀረጸባቸው ድንጋዮችና ሸክላዎች በስተቀር ምንም የታወቀ ነገር አላቀረቡም።



ሱሜሪያኖች በጣም የሠለጠኑና ከተማዎችን ቆርቁረው [illegible]ሩ ነበር። በየግዛት ከፋፍለው ይገዙዋቸው የነበሩ ነገሥታትም ነበሩአቸው። እነርሱም ካህናት መስጊዶችና የተለያዩ የአምልኮ ስፍራዎችን ሠርተው እግዚአብሔርን የሚያመልኩና ወራትን፥ ሳምንታትንና ዘመናትን የሚቆጥሩት የጨረቃንና የከዋክብትን መውጣትና መጥለቅ በመከታተል ነበር። በዘመን አቆጣጠር ስልታቸውም ልክ አሁን እኛ እንደምንጠቀምበት ሁሉ ሳምንቶቻቸው 7 ቀናትን የያዙ ናቸው፤ ዓመታቸውም 12 ወራቶችን የያዙ ነበሩ። ይህ ሕዝብ ከ3050 እስከ 2700 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በባቢሎን አካባቢ የሚኖር ነበር።

## ጥንታዊ የሴም ከተማ ግዛቶች

ጥንታዊ የሴም ከተማ ግዛቶች በባቢሎን ምድር የሚገኙ ናቸው፤ እነርሱም፦

ኢራቅ፥
አክጽንና
ካል ተብለዋል።

እነዚህ ጎሣዎችም አሹር የተባለው የሴም ዘር ዝርያዎች ነበሩ፤ ዘፍ.10፡8-12። በኋላም እነዚህ ከተማዎች ማለት በተለይም ባቢልና ሱሜሪያ ጦረኛና አዳኝ በሆነው በካም ልጅ በናምሩድ ወራሪ ኃይል ተይዘዋል። ከዚያም ናምሩድ የራሱን መንግሥት አቋቁሞ ኖረ። በኋላም ይህ መንግሥት የባቢሎን መንግሥት ተብሎ ይጠራ ጀመር፤ ዘፍ.10፡10።

ከዚያም ናምሩድ ወደ ሰሜናዊ ምሥራቅ ዘምቶ አሹርን ካባረረ በኋላ የነነዌን የርሆቦትን፥ የካልናንና የሬሳን ከተማዎች ቆርቁሮ ታላቁን የሶርያ መንግሥት አቋቋመ፤ ዘፍ.10፡11-12።

## የመጀመሪያው የዓለም መንግሥት መቋቋም

የዓለም መንግሥት ስንል በአንድ መሪ ሥር ተጠቃልሎ የሚተዳደር ራሱን የቻለ አንድ የዓለም መንግሥት ማለታችን ነው።

ከዚህ ቀጥለን በዘፍ.10፡8-12 በሚገኘው ክፍል ውስጥ በመጀመሪያ ጊዜ ዓለምን ሁሉ በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር አሰባስቦ ስለገዛው ሰው ሕይወት እናነባለን። እርሱም የኩሽ ልጅ የነበረው ናምሩድ ነበረ። እርሱ በሚገዛበትም ዘመን ሰው እግዚአብሔርን ባለማወቅ ስለተሞላ ምድር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ተበላሽታ ነበር፤ ዘፍ.10፡8፤ 6፡11።

ናምሩድም እግዚአብሔርን ይፈራ የነበረውን አሹርን ከአገሩ አሳዶ ካስወጣ በኋላ የእግዚአብሔር ተቃዋሚና ተቀናቃኝ የሆነ መንግሥትን አቋቋመ። በዚህ መንግሥትም ውስጥ ናምሩድ ራሱን እንደ አምላክ አድርጎ ስግደትና አምልኮን ይቀበል እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። እርሱም በባቢሎን ምድር ማርዱክ ተብሎ በመሰየም «የባቢሎን አምላክ» ተብሎ ሲጠራ ኖሯል።

ሰዎችን በእግዚአብሔር ላይ በማስነሣት ራሱ እንደ አምላክ እንዲመለክ ያደረገው የመጀመሪያው ሰው ናምሩድ ነበረ። በመጨረሻ ዘመን ደግሞ ራሱ አምላክ እንደሆነ እየተናገረ አምልኮን ለመቀበል ሰዎችን የሚመራው ሰው ደግሞ ሐሣዊው መሢህ የሚባል ሰው ይሆናል።

ክርስቶስ ሲመጣም ይህን ሐሣዊ መሢህ የተባለውን ሰው በእሳት ባሕር ውስጥ ይጥለዋል፤ ራዕይ 19፡11-20። በእነዚህ ሁለቱ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ በሆኑ ሰዎች ዘመን መካከል እነርሱን የመሳሰሉ ብዙ ሰዎች ተነሥተዋል።

የእነዚህ የዓለም ገዢ የነበሩ ሰዎች ጸባይ ከዚህ የሚከተለውን ይመስላል፦

1. እግዚአብሔር የዓለም ገዢ እንደሆነ ይክዳሉ፤
2. እግዚአብሔር በሚሰጠው ኃይልና ደስታ መመካትን ጨርሶ አይፈቅዱም፤
3. እግዚእብሐር ለሰዎች ያደረገውን ውለታ ራሳቸው እንዳደረጉት አድርገው ምስጋናውን ለራሳቸው ይቀበላሉ፤
4. ዓለምን በሙሉ ከእግዚአብሔር ለይተው ለራሳቸው ለመግዛት ይሞክራሉ፤
5. በእግዚአብሔር ፋንታ ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጋሉ።

ይህ ዓይነቱ ጸባይ በኃጢአት ውስጥ የወደቀ ሰው ባሕርይ ነው፤ ሮሜ 8፡7። በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ እንዲህ ያለውን ሰው አራዊት ይለዋል። በዚያን ጊዜ ልክ እንደዚህ የነበረ ሰው ባይኖርም መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ በኋለኛው ዘመን ስለሚነሣው ሐሣዊ መሢህ ስለተባለው ሰው ያስረዳናል። እርሱም በዓለም ውስጥ የሚነሣው ወደ ዓለም ፍጻሜ መጨረሻ አካባቢ ላይ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳችን ደህና አድርጎ ይገልጻል፤ 2ኛ ተሰሎ.2፡6-7፤ 2ኛ ጴጥ.3፡9፤15። ይህ ሐሳዊ መሢህ የተባለው ሰው በሚነሣበት ዘመን እርሱን መሰሎች ሁሉ ከእርሱ ጋር አብረው እንደሚጠፉ ቃሉ በትክክል ያስረዳል። ስለዚህ ወደፊት ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ስለሚመጣ ቶሎ ብለን የሚድኑትን ወደ እግዚአብሔር እንሰብስብ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስማቸው የተመለከተው ብዙዎቹ ነገሥታት ስም እንዲሁም የነገሡበት፥ በጦርነት ድል ያደረጉበትና ድል የሆኑበት ቦታዎች ስም በሸክላ ገበታዎችና በድንጋዮች ላይ ተጽፈው ተገኝተዋል። የሚበልጡትን ነገሥታት ታሪክ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይተርክልናል።

## የጥንታዊው የባቢሎን መንግሥት ታሪክ

ይህ የባቢሎን መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተው በናምሩድ ሲሆን በ2000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አካባቢ ባቢሎንን ያስተዳድሩ የነበሩት ከሴም ነገድ የተወለዱ ነገሥታት ነበሩ። ከነዚህም መካከል ስድስተኛው ንጉሥ ሆኖ የነገሠው ሐሙራቢ ነበረ። ይህንንም ንጉሥ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሰናኦር ንጉሥ ብሎ ይጠራዋል፤ ዘፍ.14፡1። እርሱም በዘመኑ ታላቅና ድል አድራጊ ንጉሥ፥ ዝናን ያተረፈና በዘመኑ ብዙ ጠንካራ መንግሥታትን አቋቁሞ እንደነበር ይነገርለታል። ዘፍጥረት ምዕራፍ 14 የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት ከሌሎች ሁለት ነገሥታት ጋር ሆነው ከሌሎች አምስት ነገሥታት ጋር ተዋግተው እንዴት ድል እንደሆኑ ይነግረናል። ከዚያም አብርሃም በሰዶም የሚኖረው ሎጥ ከሞላ ንብረቱና ከቤተሰቡ ጋር እንደተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ ከተወለዱ ሦስት መቶ ብላቴናዎች ጋር ተከታትሎ በመዝመት ምርኮኞቹንና ንብረታቸውን እንዳስመለሰ እናነባለን። ከእነዚህም በአብርሃም ድል ከተመቱት አራት ነገሥታት መካከል የጦሩ መሪና ዋነኛው አስተባባሪ የኢላም ንጉሥ የነበረው ኮሎዶጎምር ነበረ።



ከዚህ በኋላም የባቢሎን መንግሥት ለሁለት ተከፍሎ ሰሜናዊው ክፍል ሐሙራቢ ወይም አምራፌል በሚባል ንጉሥ ሥር የሚተዳደር ሲሆን ደቡባዊው ክፍል ደግሞ አርዮክ በሚባል ንጉሥ ሥር ይተዳደር ጀመር። በኋላም ሐሙራቢ የኤላምን ቀንበር ሰብሮ ባቢሎንን በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር አጠቃሎ ያስተዳድር ጀመር። ግዛቱም ከኤላም ተራራ ጀምሮ እስከ ጤግሮስ ወንዝ ከዚያም እስከ ሜዲትራኒያን ባሕር የሚደርስ ሲሆን ሶርያንና ከነዓንን ያጠቃልል ነበር።

ሐሙራቢ በዘመኑ ሀገሩን በሰላም ያስተዳደረ ንጉሥ ከመሆኑም በላይ መልዕክቱን ሁሉ በደብዳቤ በየግዛቱ የሚያስተላልፈው በሰው መልዕክተኛነት ነበረ። እርሱም በዘመኑ ጽፎቸው ከነበሩት ደብዳቤዎች መካከል ሃምሳ አምስቱ ያህል ተገኝተዋል፤ በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታና የአስተዳደሩን ዘዴዎች የሚገልጹ ናቸው።

እንደ ወረቀት ይጠቀምባቸው የነበሩት ስስ ሸክላዎች ሲሆኑ የሚጻፍባቸው ገና እርጥብ እንዳሉ ነው። ከዚያን በኋላም ሌላ ዝርግ ሸክላ እንደ ከዳን ይገጠምበትና ልክ እንደ ፖስታ ታሽጎ ወደሚመለከተው ሰው ዘንድ ጽሑፉን የያዘ መልዕክተኛ ይላክ ነበረ። ደብዳቤዎቹም እስከ ዛሬ ድረስ ሳይበላሹ ሊጠበቁ የቻሉበት በዚሁ ምክንያት ነው። ወረቀት ቢሆንማ ኖሮ ሊበላሽም ሆነ ሊበሰብስ ይችል ነበር። ሐሙራቢ ለሀገሩ መተዳደርያ አድርጎ የሰጠው ሕግ በድንጋይ ሰሌዳ ላይ ተጽፎ ተገኝቶአል። ከሕጉም ግርጌ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ነበረበት፦

«የተዛባውን ነገር ለማቃናት፥ የተበላሸውን ለማረም ይህን ከሰማይና ከምድር የከበደውን ሕጌን ባቢሎን ማርዱክና ቤል ራሳቸውን ለስግደት በሚያነሡበት በኢሰገል መቅደስ ውስጥ ሆኜ በግዛቴ ያለ ሕዝብ ሁሉ እንዲመራበት በአምዱ ላይ ጽፌዋለሁ። ስለዚህ እኔ የጽድቅ ንጉሥ ሆኜ ይህን አምድ አቁሜዋለሁ። ቃሎቼ ውድ ናቸው፤ ስሥልጣኔም ወደር የለውም፤ ታላላቅ አማልክት ለስሜ ያውጃሉ፤ እኔ ለሁሉ ደኅንነትን የምሰጥ እረኛ ነኝ።»

ሐሙራቢ በሕጉ ውስጥ «የነገሥታት አምላክ፥ የምድርና የሰማይ ብርሃናት ሁሉ ፈጣሪ እንደሆን ከመግለጹ በላይ የሰው አዳኝና መድኃኒት ነኝ» ብሎ ተናግሮአል። በዚህ ላይ እንደምንመለከተው አብዛኛዎቹ የዓለም ነገሥታትና መሪዎች በሚታበዩበት ጊዜ ዘወትር ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር ለማወዳደርና አንዳንዴም ከእርሱ የላቁ እንደሆኑ የሚሰማቸው ጊዜ አለ።

## በከለዳውያን አገር የምትገኘው የዑር ከተማ

በባቢሎን አገር ውስጥ ከኤፍራጥስ ወንዝ በስተምዕራብ የሚገኘው ከተማ ዑር ይባላል። ይህ ከተማ ብዙ የተለያዩ ሙያዎች የሚገበዩባቸው የተለያዩ ተቋሞች ያሉበት ከመሆኑ በላይ የከተማው ነዋሪዎችም እጅግ ባለጸጋዎች ነበሩ። እነርሱም በጣም ባማሩና በተጌጡ ቤቶችና ሕንፃዎች ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሲኒን የመሳሰሉ የመጠጫ ዕቃዎቻቸው ደግሞ ከከበሩ ድንጋዮች፥ ከወርቅና ከብር የተሠሩ ነበሩ። በአጠቃላይ ብዙ ዓለማውያን በሥጋ የሚመኙዋቸው ጌጣጌጦች ይገኙበት ነበር። አብርሃምም በሐሙራቢ ዘመነ መንግሥት በዚህ ከተማ ይኖር ነበር። አብርሃምና ሣራ በከተማው ውስጥ አሉ ከሚባሉት አዋቂዎችና ባለጸጋዎች መካከል እንደ አንዳንዶቹ ነበሩ። ሆኖም እነዚህ ሰዎች በከተማው ውስጥ ከነበራቸው የተንደላቀቀና ያማረ ኑሮ ይልቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ግድ ስላሳቸው ሙያቸውንና

ክብራቸውን ከምንም ሳይቆጥሩ ከእግዚአብሔር የደረሳቸውን ጥሪ ሰምተው መኖሪያቸውን ለቀው እግዚአብሔር ወደ መራቸው ለፍራ ሄደዋል። በዚያን ዘመን የሁር ከተማ ነዋሪዎች አምላክ ጨረቃ ነበር።

# ምዕራፍ ሦስት

## ግብፅ

## ጥንታዊቷ ምስር ወይም ግብፅ

ግብፅ በሊቢያና ሱዳን የምትዋሰን አገር ስትሆን ስፋትዋና ወርድዋ ሦለት ሦስት ሺህ ኪሎ ሜትር የሆነ እጅግ ለም ምድር ናት። ከዚህም በቀር ሜዲትራንያን ባሕር በስፋትዋ የሚፈስባት ውኃ ገብ መሬት ናት። የአገሪትዋም መሐከላዊ ስፍራ ዮሴፍ ወንድሞቹንና አባቱን ወደ ግብፅ አምጥቷቸው በነበረበት ጊዜ አንድ ሕዝብ እስከሚሆኑ ድረስ የሚኖሩበትን ምድር ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ከሆነ የምስር ሕዝቦች ከካም ልጅ ከምጽራይም የተወለዱ ናቸው፤ ዘፍ.10፡6። ከዚህ ስፍራ በቀር በተለያዩ ስፍራዎች ግብፃውያን የካም ልጅ የምጽራይም ዝርያዎች እንደሆኑ ተጠቅሷል፤ መዝ.78፡51፤ 105፡23፤27፤ 106፡22። እነርሱም ጥቂት ቆይተው ከሌሎች ወገኖች ጋር ተቀላቅለው በጋብቻ ተክላልሰዋል።

ግብፅ ከጥንት ዘመን ጀምራ በሥልጣኔ የታወቀችና አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ በሕንፃዎችዋና በጥንት ቅርሶችዋ እጅግ የምትደነቅ ከተማ ናት። በዚህ ላይ ስለ ጥንታዊቱ ግብፅ መተረካችንን ለጥቂት ጊዜ ቆም አድርገን በ2000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ገደማ በአብርሃምና በሐሙራቢ ዘመን ስለነበሩት የታሪክ ይዞታ እንመልከት።

## የአይሁድ አባቶች ታሪክ በምድረ ግብፅ

የሴም ነገዶች ወደ ምድረ ግብፅ የገቡት ከ2000 እስከ 1600 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት መካከል ባለው ዘመን ውስጥ ነው። እነርሱም ወደ ምድሪቷ የገቡት ቀስ በቀስ ብለው ይሆን ወይም በጦርነት ገብተው እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም። እነዚህ በምስር የሚኖሩ የሴም ነገድ ነገሥታት በዚያን ዘመን የምድረ በዳ ልዑላን ወይም እረኛ ነገሥታት እንዲሁም «ሄክሶስ» በመባል ይታወቁ ነበር። እነዚህ ሄክሶስ የተባሉት የሴም ነገዶች እንደ እግዚአብሔር እቅድ መሠረት በዮሴፍ በኩል የያዕቆብ ልጆች ሁሉ ወደ ምስር በመጡ ዘመን እነዚህ ግብፃውያን ያልሆኑ ሰዎች ለ400 ዓመታት በግብፅ ገዢዎችና ቢትወደዶች ሆነው ኖረዋል። ጥንታዊ የግብፅ ገዢዎች አስተዳዳሪዎች ቢሆኑ ኖሮ እረኞችን ይጠሉና ይጸየፉ ስለነበረ አይሁዶች በዚያ እንዲኖሩ ፈጽሞ አይፈቅዱም ነበር፤ ዘፍ.43፡32፤ 46፡34።

አይሁዶች ለ400 ዓመታት በግብፅ ከኖሩ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ምድር ሊያስገባቸው ሌላ እቅድ አወጣላቸው። ያን ዘመን በግብፅ ብዙ ምቾትና ታላቅ ብልፅግና



ስለነበረ እነዚህን ሰዎች ከዚህች ምድር እንዲወጡ ማድረግ ቀላል አልነበረም። ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከዚህ ከተደላደለ ስፍራ ማውጣት ቀላል አለመሆኑን ያውቅ ስለነበረ ዮሴፍን የማያውቁ አዳዲስ ነገሥታትን 1600-1350 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት መካከል በግብፅ አስነሥቶ አይሁዶችን እጅግ እንዲያስጨንቋቸውና እንዲያስጠብቡአቸው አደረገ። እግዚአብሔር ያስነሣቸው እነዚህ ነገሥታት በአይሁዶች ላይ አይለው በእነርሱ ቦታ በመተካት ሕዝቦችን ያስተዳድሩ ነበር። እነርሱም የጥንታዊቱ ግብፅ ዝርያዎች ሲሆኑ እስራኤላውያንን ባርያዎች አድርገው ያስጨንቋቸው ነበር። እነርሱም ግዛታቸውን ከአባይ ወንዝ አንሥቶ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ አስፋፉ።

ሙሴና አሮን ወደ እነዚህ አዳዲስ ነገሥታት መካከል ተልከው አንዱን «የእስራኤል አምላክ ሕዝቤን ልቀቅ» ይላችኋል አሉት። እርሱም፡- «ቃሉን እንድሰማ እስራኤልንስ እንድለቅቅ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም» ብሎ መልስ ይሰጣል። ይህ ነገር የተፈጸመው በ1491 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ገደማ ነው።

በምቾት ምክንያት እስራኤላውያን ከግብፅ መውጣትን እንደማይፈቅዱ እግዚአብሔር ቢያውቅም እነርሱን ለማስወጣት የሚያስጨንቅ መንግሥት ቢያስነሣም ቅሉ አሁን ደግሞ እርሱ ራሱ ጉልበታቸው ስለጣመው እንዲለቃቸው እምቢ ስላለ እግዚአብሔር በመቅሰፍት መታው።

# ምዕራፍ 4

## ከአብርሃም እስከ ሙሴ ድረስ ያሉት የእስራኤል አባቶች አለቆች

የአብርሃም ዘር ሐረግ በዘፍጥረት 11፡10-32 ባለው ክፍል ውስጥ ተዘርዝርአል። የአባቶቹም አለቆች ሕዝቡን በመሳፍንትነትም ሆነ በሃይማኖት መሪነት ያገለግሉ ነበር። አሁን በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናትተው ስለ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብና 12ቱ ልጆቹ ሲሆን በተለይም ይበልጥ የምናተኩረው በዮሴፍና በሙሴ ታሪክ ላይ ይሆናል።

የአባቶች አለቃ የነበረው የአብርሃም አባት ታራ ገና በውር ከተማ ሳለ ከአብርሃም በቀር ሌሎች ናሆርና ሐራን የተባሉ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት። ከነዚህም መካከል ሐራን የተባለው ልጁ ገና በወጣትነት ዕድሜው ሞተበት። የዑር አገር ነዋሪዎች ሁሉ ጣዖት አምላኪዎች ስለነበሩ ከተማይቱ በተለያዩ ጣዖታት ተሞልታ ነበር። በተለይም ሕዝቡ እንደ አምላክ አድርገው የሚያመልኩት ፀሐይን ስለ ነበረ በዚያን ዘመን እውነተኛውን አምላክ አውቆ የሚሰግድለት አንድም ሰው አልነበረም። በዚያን ዘመን የዑር ከተማ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው ዓለም እውነተኛውን አምላክ የማያውቅ ጣዖት አምላኪ ሕዝብ ብቻ ነበረ። እንግዲህ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደሆነና ለአገልግሎትም እንደመረጠው ያስታወቀው በዚሁ ዘመን ነበረ። እንግዲህ አብርሃም እግዚአብሔርን ለማገልገል ፈቃደኛ ሆኖ እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ የትውልድ አገሩን ለቆ

የወጣው ከዚህ በኋላ ነው። አብርሃም በፈቃዱ እግዚአብሔርን ለማገልገል በወሰነ ጊዜ እግዚአብሔር በዘሩ ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የዓለም አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩና የእርሱም ትውልዶች የዚህ የምስራች አብሳሪ አገልጋዮች እንደሚሆኑ መመረጣቸውን ያስታውቃል።

እግዚአብሔርም አብርሃምን ከከለዳውያን አገር ከዑር ከተማ ካስወጣው በኋላ ከሕዝቡ ተለይቶ በአሕዛብ መካከል እንዲቀመጥ ያዘዋል፤ ዘፍ.11፡31። ከዚህ በኋላም እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜያት ለአብርሃም ተገልጦ አነጋግሮታል። ይኸውም፡-

1. በዑር ፡- የሐዋ.7፡2፤ ዘፍ.11፡31።
2. በካራን፡- ዘፍ.12፡1-4።
3. በሴኬም፡- ዘፍ.6-7።
4. በቤቴል፡- ዘፍ.13፡14-17።
5. በኬብሮን፡- ዘፍ.15፡18፤ 17፡1-8።

እግዚአብሔር አብርሃምን ወደሚያሳየው ምድር እንዲወጣ ባዘዘው ጊዜ ወላጅ አባቱ ታራና ወንድሙ ናሆር ከዑር አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቃ እስከምትገኘው እስከ ካራን ድረስ አብረውት መጡ፤ በኋላም እግዚአብሔር እንደገና አብርሃምን ከካራን እንዲወጣ በጠየቀው ጊዜ ወንድሙና አባቱ በዚያው በካራን ሲቀሩ የወንድሙ ልጅ ሎጥ አብሮት ከካራን ወጣ። በኋላም የአብርሃም ልጅ ይስሕቅና የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ ሚስትን ያገቡት ከአብርሃም ወንድም ከናሆር ቤተሰብ ነበረ። እነርሱም በዙሪያቸው ካሉ ከአሕዛብ መካከል ለራሳቸው ሚስቶችን ያላገቡት አንደኛው ምክንያት በዙሪያቸው ያሉት አሕዛብ ጣዖት አምላኪዎች ስለሆኑና ልጆቻቸውን የጣዖት አምልኮን በማስተማር ከእውነተኛው አምላክ እንዳያርቋቸው ነው። ሌላው ምክንያታቸው ደግሞ ልክ እንደ እነርሱ እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ወገኖች ሚስት ቢያገቡ እንደዚህ ባለው መሰናክል ውስጥ እንደማይገቡ ስላወቁ ነበር።

አብርሃም ከነዓን በደረሰ ጊዜ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን 50 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ሴኬም በተባለች ሥፍራ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠርቶ በዚያ መኖር ጀመረ፤ ዘፍ.12፡6። ከዚያ በኋላ በተሰፋው ቃል መሠረት 600 ዓመት ቆይቶ ኢያሱ የከነዓንን ምድር ወረሰ። ከዚያም አብርሃምም በከነዓን ምድር ከሴኬም ከተነሣ በኋላ የሠፈረው ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን 15 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኝ ቤቴል በምትባል ስፍራ ነው። አሁንም አብርሃም ወደ ቤቴል እንደመጣ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ፤ ዘፍ.12፡8። አብርሃምና ሎጥ የተለያዩበትም በዚያው ነበር። በኋላም ያዕቆብ ከሰማይ እስከ ምድር የሚደርስ ሰማያዊ መሰላል ተተክሎ የተመለከተው በዚሁ ስፍራ ነበረ። በኋላም ውሎ አድሮ በአንድ በተወሰነ ዘመን ውስጥ ቤቴል የበሜናዊው መንግሥት የጥጃ ጣዖት ማምለኪያ ማዕከል ተደረገች።

የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ ዋና መኖሪያ ስፍራቸው ከኢየሩሳሌም 30 ኪሎ ሜትር በስተ ደቡብ ርቃ በምትገኘው በኬብሮን ነበረ። ይህች ከተማ በኢየሩሳሌም ከነበሩት ከተማዎች ሁሉ ጥንታዊቷና የመጀመሪያዋ ናት። ዳዊትም ለሰባት ዓመት የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ የነገሠው በዚህችው ከተማ ነበረ። አብርሃም በሕይወት በነበረበት ዘመን የኢየሩሳሌም ከተማ እምብዛም አትታወቅም ነበር። በዚያን ዘመን ካህንና ንጉሥ የነበረው መልከ ጼዴቅ ይኖርባት ስለነበረ ሳሌም በመባል ብቻ ትታወቅ ነበር፤ ዘፍ. 14፡18።



አብርሃምም በከንዓን ምድር ማለት በቤቴል በሴኬምና በኬብሮን ሦስት መሠዊያዎችን ሠርቶ ነበር። ይኸውም በዚያን ዘመን ለነበሩ ለጣዖት አምላኪዎች እርሱ እውነተኛውን አምላክ እንደሚያመልክ ምስክር እንዲሆንባቸው ነው።

አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ አብዛኛውን የሕይወት ዘመናቸውን ያሳለፉት ከኬብሮን 38 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገናው ቤርሳቤህ ተብላ በምትጠራ ስፍራ ነበረ። በምድሪቱም ላይ ረሃብ በሆነበት ጊዜ አብርሃም ወደ ምስር ሄደ። ሆኖም ብዙ ሳይቆይ ወዲያውኑ ወደ ቤቴል ተመልሷል፤ ዘፍ.12፡10-20፤ 13፡1-4። በእረኞቻቸው መካከል ጠብ በሆነ ጊዜ አብርሃምና ሎጥ የተለያዩት በዚሁ ስፍራ ነበረ። አብርሃም ሎጥን እኔና አንተ ወንድማማች ስለሆንን ልንጣላ አይገባንም፤ ስለዚህ አንተ ቀኙን ብትመርጥ እኔ ግራውን ከፍል እወስዳለሁ፤ አንተ ፊተኛውን ብትመርጥ እኔ ኋለኛውን እወስዳለሁ ብሎ ምርጫ በሰጠው ጊዜ ሎጥ ይህንን እጅግ ለም ስፍራ የመረጠው በዚህን ጊዜ ነበረ። እነዚህ የሰዶም ሰዎች በጣም በኃጢአት የተበከሉና ከተሞቻቸውም በእርኩሰት የተዋጡ ነበሩ። ሎጥ እጅግ አድርጎ ገንዘብንና ብልጽግናን ይወድ ስለነበረ ከእነዚህ ሕዝብ መካከል መኖርን ከቶ አልፈራም። ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሁሉ ሥር ስለሆነ ሎጥ የወደደውን ሀብትና ብልጽግና ብዙ ሳይጠቀምበት በፊት የተነጠቀው ለዚህ ነበር፤ 1ኛ ጢሞ.6፡10። ሎጥ እንደ ጣዕት ያመልከው የነበረውን ብልጽግና ኮሎዶጎመር ከእርሱ ጋር አራት ሌሎች ነገሥታትን አስተባብሮ ሰዶምንና ጎመራን በወጋት ጊዜ ሎጥንና ቤተሰቡን ያለውን ሀብት ጭምር ማርኮ ወስዶአል። አጎቱ አብርሃምም ይህንን ሁኔታ በሰማ ጊዜ በቤቱ የተወለዱትን 318 ብላቴናዎችን አስከትሎ ከኮሎዶጎመርና ከጭፍራዎቹ ሁሉ ጋር ድል አድርጎ ምርኮ ከመማረኩም በላይ ሎጥንና ቤተሰቡን ከነንብረቱ አድኖአል። እግዚአብሔርም በነገሥታቱ ላይ በሰጠው ድል ምክንያት አብርሃም በሕዝቡ ፊት እንደ ታላቅ ሰውና እንደ ኃያል መስፍን ሳይቆጠር አልቀረም፤ ዘፍ.14፡1-17።

አብርሃም ከጦርነት ሲመለስ የሳሌም ንጉሥና ካህን የነበረው መልከጼዴቅ አብርሃምን ተቀብሎ ባረከው። መልከጼዴቅ ከአብርሃም በፊት በሳሌም ከተማ የኖረ ስለ እግዚአብሔር ይመሰክር የነበረ ሰው ሳይሆን አይቀርም፤ ዘፍ.14፡18-24። መልከጼዴቅ የክርስቶስ ምሳሌ ስለነበረ የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ይባል ነበረ፤ ዕብ.7። ሳሌም የዳዊት ዋና ከተማ የነበረችውና በኋላም ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ኢየሩሳሌም ተብላ የተሰየመችው ናት። ክርስቶስም የነገሥታት ንጉሥ እንደ መሆኑ ሁሉ በመጨረሻው ዘመን በምድር ለሺህ ዓመት ሊነግሥ ይመጣል።

የሰዶምና የገሞራ አገር የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው መልከጼዴቅ ከሚኖርበት ሥፍራ 30 ኪሎ ሜትር ርቀው ቢገኙም የሕዝባቸው ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ስለከፋ እግዚአብሔር ከሰማይ ዲን አውርዶ ደምስሶአቸዋል። በእነዚህ ከተማዎች ውስጥ ከሚኖሩት መካከል ካለ ሎጥና ሁለት ልጆቹ በቀር ማንም አልተረፈም። የሎጥ ልብ ደግነትን ብቻ የሚወድ ቢሆንም እንኳ በዚህን ጊዜ ምንም ሳይተርፍለት ሁሉንም ነገር አጥቷል፤ ዘፍ.19።

ሁለቱም የሎጥ ሴቶች ልጆች አሞንና ሞአብ የተባሉ ወንዶች ልጆችን ወለዱ። እነርሱም አሞናውያንና ሞአባውያን የተባሉ የሁለቱ ጉሳዎች አባቶች ናቸው፤ ዘፍ.19፡30-38።

አብርሃምም የሣራ ገረድ ከነበረችው አጋር ከተባለችው ግብፃዊት እስማኤል የተባለውን ልጅ ወለደ፤ ዘፍ.16። ሳራ ከሞተች በኋላ አብርሃም ካገባት ኬጡራ ከተባለች ሴት ምድያም የተባለውን የምድያማውያንን አባት ወልዶ ነበር። ያም ሆነ ይህ ዞረው ዞረው እነዚህ ሁሉ ጐሳዎች የተስፋው ልጅ ዘር በሆኑት በእስራኤላውያን ላይ ደመኛ ጠላት ሆነውባቸዋል። በተለይም አረቦች ምንም የአብርሃም ልጆች ቢሆኑም እስከ ዛሬ ድረስ የእስራኤላውያን ዋና ጠላቶች እንደሆኑ ይኖራሉ። እግዚአብሔር አንድ ብቻ እንደሆነ የሚያስተምሩ ሦስት ሃይማኖቶች ይገኛሉ። እነርሱም:- የአይሁድ ሃይማኖት ክርስትና እና እስልምና ናቸው።

እግዚአብሔርም በስተርጅናው ለአብርሃም ወንድ ልጅ እንደሚወለድለት ተስፋ ሰጠው። ይስሐቅ በተወለደ ጊዜም አብርሃም የመቶ ዓመት ሲሆን ሚስቱ ሣራ ደግሞ የ90 ዓመት ሰው ነበረች። ከዚያም በኋላ አብርሃም መቶ ሰባ አምስት ዓመት ዕድሜ እንደሆነው ሞተ።

## እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን

1. ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገውና እንደሚባርከው ስሙንም እንደሚያከብረው፤ ዘፍ.12፡1-3።
2. የከነዓንን ምድር እንደሚያወርሰው፤ ዘፍ.12፡7።
3. ከነዓንን ለዘለዓለም ለዘሩ እንደሰጠ፤ ዘፍ.13፡15-16።
4. ዘሩን እንደማይቆጠሩ ከዋክብት እንደሚያበዛ፤ ዘፍ.15፡5።
5. የነገሥታትና የአሕዛብ አባት እንደሚያደርገው፤ ዘፍ.17፡1-6።

ይስሐቅም ሚስት ባገባበት ጊዜ የ40 ዓመት ሰው ነበረ። እርሱም ሚስትን ያገኘው የሁለት ወንዝ መካከል ተብሎ ከሚጠራው ከሚሶጶጦሚያ ሲሆን ልዩ ስፍራውም ካራን ይባላል። እርሰዋም የአብርሃም ወንድም የናሆር የልጅ ልጅ ነበረች። ስምዋም ርብቃ ይባል ነበር። ይስሐቅም በእግዚአብሔር የምታምነውን ልጅ አገባ።

ይስሐቅም ያዕቆብና ኤሳው የሚባሉትን ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ። እግዚአብሔርም ያዕቆብን የእስራኤላውያን ሁሉ አባት እንዲሆን መረጠው። ኤሳው ግን በእግዚአብሔር ከማያምኑ ከአረማውያን ወገን የሆነች ሴት አግብቶ በሴይር አገር ተቀመጠ። እርሱም በዘመናት ሁሉ የእስራኤላውያን ጠንቀኛ ጠላት የነበሩት የኤዶማውያኖች አባት ሆነ። አባታቸው ይስሐቅም በመቶ ሰማንያ ዓመት ዕድሜው ሞተ፤ ዘፍ.21።

ያዕቆብ ወንድሙንና አባቱን በመሸንገሉ ሕይወቱን ለማዳን መኮብለል ነበረበት። በዚህም ምክንያት በሁለቱ ወንዞች መካከል ወደሚገኘው ወደ አጐቱ ዘንድ ሄዶ በሜሶጶታሚያ መኖር ጀመረ። እርሱም በዚያ በኖረበት ዘመን ሁሉ ሁለት ልጆቹንና በጐቹን ለማግኘት አጐቱን ላባን 20 ዓመት ሙሉ አገልግሎታል። የያዕቆብ ዝርያዎች 12 ነገዶች ሊሆኑ የቻሉት 12 ወንዶች ልጆች ወልዶ ስለነበረ ነው። ያዕቆብም በሞተ ጊዜ መቶ አርባ ሰባት ዓመት ሆኖት ነበረ፤ ዘፍ.40፡28። እግዚአብሔር አብርሃምን የብዙ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን የገባለት ቢሆንም የተስፋው ልጅ ይስሐቅ ለአብርሃም የተወለደለት አብርሃም የመቶ ዓመት ሽማግሌ በነበረበት ጊዜ ነው። ይስሐቅ ያዕቆብ በተወለደለት ጊዜ የ60 ዓመት ሰው ነበረ። ልጁ ያዕቆብ ባገባበት ጊዜ ደግሞ 70 ዓመት ሆኖት ነበረ። ይስሐቅ ለአብርሃም ቀደም ብሎ



ተወልዶለት ቢሆን ኖሮ እርሱ በተወለደበት ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ጥቂት ተባዝቶ በሆን ነበር። ከዚህ በኋላ ግን የእስራኤል ሕዝብ ተበራክቶ አንድ ታላቅ ሕዝብ እስኪሆን ድረስ የ400 ዓመት ጊዜ ወስዶበታል።

አመጸኞችና ለእግዚአብሔር የማይታዘዙትን ከነዓናውያንን ከምድራቸው አስወግደው እንደ ተስፋ ቃሉ እስራኤላውያን ምድሪትዋን እንዲወርሱ እግዚአብሔር በከነዓናውያን ላይ ፈርዶባቸዋል። ቢሆንም ይህ ፍርድ ከነዓናውያን ዝከረ መታሰቢያቸው ከምድር ላይ እስከሚጠፋ ድረስ አልነበረም። እግዚአብሔር ለከነዓናውያን ረጅም የንስሐ ጊዜ ሰጥቶአቸዋል። ያም ሆነ ይህ እስራኤላውያንን በከነዓናውያን ላይ የፍርድ ጅራፍ አድርጐ ለመጨረሻው ቀን ጠብቆአቸዋል። እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን ለነበሩት ሰዎች 120 ዓመት የንስሐ ዘመን እንደሰጣቸው ሁሉ ከነዓናውያንንም ብዙ የንስሐ ዘመን አልነፈጋቸውም፤ ዘፍ.15፡16። ይህንን ዕድል ባይጠቀሙ ግን እግዚአብሔር በእስራኤላውያን በኩል ፍርዱን ሊያመጣባቸው ወስኖአል።

<u>ዮሴፍ</u>:- እግዚአብሔር የያዕቆብን ልጆች በሙሉ እንደ አንድ ሕዝብ አድርጐ ሊያበዛቸው ስለወደደ ዮሴፍ ሰብሳቢያቸው እንዲሆን አስቀድሞ ወደ ግብፅ እንዲሄድ አድርጐለታል። ዮሴፍ በወንድሞቹ እጅ ለምስር ነጋዴዎች ተሸጦ የሄደ ቢሆንም በዓላማው ውስጥ የእግዚአብሔር እጅ ስለነበረበት ዮሴፍ በግብፅ ብዙ ዘመን ከመቆየቱ በፊት ከፍ ከፍ ብሎ ከፈርዖን በታች ምክትል አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ። በዚህን ጊዜ ዮሴፍ አባቱንና ወንድሞቹን ከነቤተሰቦቻቸው ሁሉ ጋር አድርጐ በግብፅ ምድር ጌሴም በሚባልበት ሥፍራ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

የያዕቆብ ዘሮች በግብፅ በሚኖሩበት ጊዜ እግዚአብሔር ሄክሶስ የተባሉትን የነገሥታት ዘሮች አስነሥቶላቸው ታላቅ ወዳጅ እንዲሆኑዋቸው አድርጐላቸዋል። በግብፅ የነገሥታት ዘሮች የከብት እረኛ የሆኑትን ወገኖች ይጸየፉአቸው ስለነበረ አይወዱአቸውም ነበር። በዚህ ምክንያት እረኞች የነበሩትን እስራኤላውያን ግብፃውያኖች ይጠሉአቸው ነበረ፤ ዘፍ.43፡32 እና 46፡34።

ያዕቆብ ወደ ግብፅ ሲወርድ ከነቤተሰቡ 70 ነፍስ ሆኖ ነበር፤ ዘፍ.46፡26-27። እግዚአብሔር ይህንን ቤተሰብ የመረጠውና መሢሑ ክርስቶስም ከእነርሱ እንዲወለድ ያቀደው ገና ከጥንት ጀምሮ ነበረ።

እግዚአብሔር ለአባታቸው ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት የያዕቆብን ቤተሰብ በግብፅ ምድር በ400 ዓመት ውስጥ ታላቅ ሕዝብ ካደረጋቸው በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ማለት ወደ ከነዓን እንደሚያስገባቸው ዮሴፍ ያምን ነበረ፤ ዘፍ.15፡13-15። ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል ሕዝቡን ወደ ከነዓን ሊያስገባቸው እንደሚችል አምኖ ዮሴፍ በሞተ ጊዜ ልጆቹ አጥንቱን ይዘው እንዲሄዱ አምሎአቸዋል፤ ዘፍ.50፡24-25፤ ዘፀ.13፡19። ዮሴፍ በሞተ ጊዜ ዕድሜው 110 ዓመት ሆኖት ነበር፤ ዘፍ.50፡26። እስራኤላውያንም የግብፅን ምድር ለቀው በወጡ ዕለት የዮሴፍን አጥንት ተሸክመው በሴኬም ቀበሩት፤ ኢያሱ 24፡32።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ባወጣቸው ዕለት ሙሴ መሪያቸው እንዲሆን ሰጣቸው። በዚያን ዘመንም የከነዓናውያን ኃጢአት ከመጠን አልፎ የጥፋት ፍርድ

ብቻ ቀርቶላቸው ነበር። እስራኤላውያን በግብፅ በሰላም የኖሩት ሂክሶስ የተባሉት የጥንት ነገሥታት በሚያስተዳድሩበት ዘመን ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ግን እስራኤላውያንን ከግብፅ የማስወጣቱ ወራት በደረሰ ጊዜ አይሁድን ይጠሉ የነበሩትን የምስር ገገርዎች እስነሥቶ እንዲያሠቃዩአቸው አደረገ፤ ዘፀ.1፡8። በመውጫቸው ዘመን ግብፅን ያስተዳድር የነበረው የምስር ንጉሥ እስራኤላውያንን አጥብቆ ይጠላ ስለነበር እጅግ ያስጨንቃቸው ነበር፤ ዘፀአት ምዕ. 1 በሙሉ አንብቡ። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ መርቶ ከማስወጣቱ በፊት በፈርዖን ቤትና በምድያም አገር ደህና አድርጐ እንዲሰለጥን እግዚአብሔር አጋጣሚ ሁኔታን ፈጥሮለት ነበር። ሙሴ የምድረ በዳን ኑሮ ተለማምዶ ስለነበረ የእስራኤልን ሕዝብ በምድረ በዳ ለ40 ዓመት ቀጥ አድርጐ መርቶአቸዋል። በዚህ ጉዞ ውስጥም የእስራኤል ንጉሥና አምላክ የሆነው ክርስቶስም ባጋጠማቸው ችግር ሁሉ በመድረስ ተአምራት እየሠራ ፍላጐታቸውን በማርካት ራሱን ያስተዋውቃቸው ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ከነዓን የመራቸው በቀጥታ ሳይሆን በምድረ በዳ ውስጥ እያዘዋወረ ነበር። ይህን ያደረገበት ምክንያት ሕዝቡ እንዲያውቁትና በእርሱ መተማመንን እንዲማሩ ብሎ ነው። እነርሱም በገጠማቸው ችግሮች ውስጥ ስለ ምግብ፥ ውኃና ልብስ እንዲሁም በጦርነት ድል ለማግኘት በእርሱ መተማመንን ተማሩ። እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ አሳልፎአቸው ወደ ተስፋይቱ ምድር አቅራቢያ ሲያደርሳቸው በምድሩ ውስጥ ይኖሩ በነበሩት ኃያላን ሰዎችም ላይ ድል እንደሚያጐናጽፋቸው አመኑበት።

የእስራኤል ልጆች ከግብፅ በወጡ ጊዜ ከሴቶችና ከሕፃናት በቀር ሰልፈኞች ብቻ 600000 ያህሉ ነበር። ሴቶችንና ልጆችን ጨምሮ ግን ሁሉም በአጠቃላይ ወደ ሦስት ሚሊዮን ሳይሆኑ አይቀሩም። ሙሴ ይኸንን ሁሉ ሕዝብ ያለ እግዚአብሔር ዕርዳታ በምድረ በዳ 40 ዓመት ሊመራቸው ይችላል ማለት ዘበት ነው። ስለሆነም በእግዚአብሔር ዕርዳታና ቸርነት ይህን አገልግሎት ሊፈጽም በቅቶአል።

ሙሴም ሕዝቡን አስጉዞ በሲና ምድረ በዳ በኩል ወደ ሲና ተራራ ሲመጣ ሕዝቡን ከሌላ ሕዝብ ለይቶ የእግዚአብሔር እንዲሆኑ የሚያደርጋቸውን ሕግ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ሰጥቶአቸዋል።

# ምዕራፍ 5

አሁን የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በጉዞ ላይ ሳለ በኤዶም ምድር አቅጣጫ አልፎ የሎጥ ልጆች የነበሩትን የሞአብንና የአሞንን ምድር አቋርጦ መሄድ ነበረበት። ቢሆንም አሞናውያንና ሞአባውያን በምድራቸው አቋርጦ እንዲያልፍ አልፈቀዱለትም ነበር። ሆኖም በሌላ መንገድ አድርጐ ጉዞውን ቀጥሏል። አሁን እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት እየተቃረበ ሳለ በስውር ይመራቸው የነበረው ንጉሥ ክርስቶስ በእርሱ ይታመኑ የነበሩትን አዲሶቹን ትውልዶች ከ40 ዓመት በፊት ለአባቶቻቸው ወደ ማለላቸው ምድር አያስገባቸው ነው። ከዚህ በኋላ እስራኤል ቀደም ሲል በተስፋይቱ ምድር የነበረውን ሕዝብ በጦርነት ከምድሩ አስወጥቶ ከወረሰ በኋላ በመሳፍንት ይተዳደር ጀመር። አሁን የእስራኤል ሕዝብ ዐግ የተባለው የባሳን ንጉሥ ያስተዳድረው የነበረውን ከዮርዳኖስ ማዶ የነበረውን ምድር በጦርነት አስለቅቆ ለሮቤል፥ ለጋድና ለምናሴ እኩሌታ እርስት ሆነ፤ ዘዳ.2፡24-3፡11



ያለውን ክፍል ተመልከቱ። የባሳን ምድር እጅግ ለምለምና ውኃ ገብ መሬት ከመሆኑ በላይ ነዋሪዎቹም በጣም ጀግኖችና ኃይለኞች ነበሩ፤ ዘዳ.32፡13-14፤ መዝ.135፡10-12፤ 136፡17-22።

<u>የሙሴ ሞት</u>፡- ሙሴ ከመሞቱ አስቀድሞ በምድረ በዳ ከነበረው አለት ውኃ እንዲፈልቅ ተናገረው ባለው ጊዜ በሕዝቡ ተቆጥቶ አለቱን በዱላ መትቶ ያልታዘዘውን በማድረጉ እግዚአብሔር በሕዝቤ ፊት አላከበርከኝም ብሎ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገባ ከለከለው። ሆኖም የተስፋይቱን ምድር በኔባል ተራራ ላይ ሆኖ ካሳየው በኋላ ሙሴ በዚያው ስለ ሞተ እግዚአብሔር ራሱ ቀብሮታል፤ ዘዳ.34። ከዚህ በኋላ ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ መሪ እንዲሆን ተመረጠ፤ እግዚአብሔር በኃይሉና በድል አድራጊነቱ የዮርዳኖስን ወንዝ ከፊታቸው ከፍሎ ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ኃይልና አጋር ሆኖለታል።

ኢያሱም ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር ይዞ ከገባ በኋላ የምድሩን ሕዝብ ድል አድርጐ ርስቱን አከፋፍሎ ለየነገዱ ሰጥቶአቸዋል። አሁን እግዚአብሔር የተስፋው ልጅ ማለት መሢሁ ኢየሱስ ሊወለድበት ያለውን ምድር አውርሷቸዋል። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ አንድ ከመሆኑ በላይ በስውር የሚመራውን ንጉሡን ክርስቶስን በሚገባ አውቆአል። የኢያሱን መጽሐፍ ብታነቡ 12ቱ የእስራኤል ነገድ ከያዕቆብ ቤት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑን ትረዳላችሁ። የአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ አባቶች ስምም፡- ሮቤል፥ ጋድ፥ ስምዖን፥ ይሁዳ፥ ዳን፥ ብንያም፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፥ አሴር፥ ንፍታሌም፥ ሌዊና አንዱ የዮሴፍ ልጅ ነው። ከያዕቆብ ልጆች መካከል አንዱ ሌዊ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተለየ በመሆኑ ከተቀሩት ነገዶች መካከል እንደ አንዱ ተቆጥሮ ርስትን አልተካፈለም ነበር። ምክንያቱም ለሌዊ ርስቱ እግዚአብሔር ራሱ ነው። ስለዚህም በሌዊ ምትክ አንዱ የዮሴፍ ልጅ ሲጨመር የእስራኤል ነገድ በጠቅላላው 12 ይሆናል ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም በዮሴፍና በሌዊ ፋንታ ሁለቱ የዮሴፍ ልጆች ከአሥራ ሁለቱ ነገዶች መካከል ገብተው የሚቆጠሩበት ጊዜ አለ።

እግዚአብሔር እስራኤል የከነዓንን ምድር ባወረሰው ጊዜ ልጆችዋ ከከነዓናውያን ጣዖቶች አምልኮ እንዳይማሩና መቅሰፍት እንዳይመጣባቸው ሲል የከነዓናውያንን ዝክረ ነገር ከምድር እንዲያጠፉ አዝዋቸው ነበር። ይህ ካልሆነ እስራኤል አንድ ሕዝብ ሆኖ በአንድነት የመኖሩ ተስፋ ይቀርበታል። ያም ሆነ ይህ በዚህን ጊዜ እስራኤል በአሕዛብ ጣዖታት ስለተጠመደ ለዓለም ሕዝብ ጥሩ ምሳሌና አርአያ መሆን አልቻለም። እርሱም እግዚአብሔር ያዘዘውን ትዕዛዝ ስላልተቀበለ የምድሩ ነዋሪዎች በሕይወት ሊኖሩ ተቶአቸዋል። በኋላም እስራኤል በጣዖት አምልኮ የታወቀ በመሆን አብዝቶ እግዚአብሔርን ስላሳዘነ እግዚአብሔር በባዕድ እጅ ማለት በባቢሎናውያንና በሶርያውያን እጅ ምርኮኛ አድርጐ ሰጥቶታል።

## <u>የእስራኤል ጐረቤቶች</u>

ሞአባውያን፥ አሞናውያን፥ ኤዶማውያን፥ አማሌቃውያን፥ ምድያማውያን፥ ፍልስጥኤማውያንና ፊንቄያውያን ናቸው።

ሞአባውያን የአብርሃም የወንድም ልጅ የሎጥ ዝርያዎች ናቸው። እነርሱም ከጨው ባሕር ምሥራቅ በሚገኘው ምድር ይኖሩ ነበር። አንድ ጊዜ እስራኤላውያን የሞአብን ምድር

ለመንጠቅ አስበው ሳለ እግዚአብሔር ይህን እንዳያደርጉ ከልክሎአቸዋል። ሞአባውያን በመሳፍንት ዘመን በእስራኤል ላይ አምፀውባቸው ስለነበር ሳኦል ብድራትን ለመክፈል አስጨንቋቸው ነበር። ስለዚህ ሞአባውያን በእስራኤል ላይ ከማመፃቸው በቀር ጣዖት አምላኪዎች ሆነው አሕዛብ ሁሉ ላመለኩት ካሙሽ ለተባለው ጣዖት አምልኮና ስግደት ይቀርቡ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር የምሕረቱ ባለጸጋነት እጅግ የበዛ ስለሆነ ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን ሲመፈጸምና በዘሩ የዓለምን አሕዛብ ለመባረክ መሢሁ ክርስቶስ ከዘርዋ ግንድ እንዲወለድ የሞአብ ተወላጅ የሆነችውን ሩት መርጧል፤ ዘኍ.21:29፤ መሳ.11:24፤ 1ኛ ነገ.11:7-33፤ ኤር.48:7።

አሞናውያን ልክ እንደ ሞአብ የሎጥ ዝርያዎች ነበሩ። ርስታቸውም ከሞአብ በስተሰሜን ሆኖ ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ 50 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝ ስፍራ ላይ ነበረ። እግዚአብሔር እስራኤል የሞአብን ምድር ለመንጠቅ እንደ ቃሉ በነበረበት ወቅት ምድራቸውን እንዳይነኩባቸው ከልክሎአቸዋል። በመሳፍንት ዘመን አሞናውያን በእስራኤላውያን ላይ ጦርነት በማስነሣት ያስጨንቋቸው ነበር። በኋላም በናቡከደነፆር ዘመን የእርሱ አባሪ በመሆን ለአይሁድ ጥፋት ረዳቶች ነበሩ። ከዚህም በቀር አይሁድ ከባቢሎን ምርኮ ወደ አገራቸው ተመልሰው ኢየሩሳሌምን እንዳያድሱ እንቅፋትና መሰናክል ሆነውባቸው ነበር፤ ነህ. 4:7። እነዚህ አሞናውያን ልጆቻቸውን ለእሳት አሳልፈው በመስጠት ያመልኩት የነበረ ሞሎክ የሚባል ጣዖት ነበራቸው፤ ዘሌዋ.18:21፤ 20:2-4፣ ኤር.32:34፤ 1ኛ ነገሥ.11:7፤ 2ኛ ነገሥ.23:10። <u>ኤዶማውያን የኤሳው</u> ዝርያዎች ናቸው፤ ዘፍ.36:9። እነርሱም በጨው ባሕር በስተደቡብ በኩል በቀይ ባሕር ሰሜናዊ ክፍል በሚገኝ ምድር የሚኖሩ ነበሩ። እስራኤላውያን ከግብፅ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ አገር በሚጓዙበት ጊዜ እነዚህ ነገዶች በምድራቸው አልፈው እንዳይሄዱ ከለከሉአቸው። በዚህን ጊዜ ሙሴ ሊዋጋቸው ሲያስብ እግዚአብሔር ከልክሎታል። ከዚያ ዘመን ጀምሮ እስከ ሳኦል ዘመን ድረስ እስራኤልም ከኤዶም ጋር ምንም ዓይነት ውጊያ አላደረገም ነበር። ከዚያን በኋላም እግዚአብሔር በበለአም አፍ እንደተናገረው ዳዊት ከኤዶማውያን ጋር ተዋግቶ ድል አድርጓቸዋል፤ ዘኁል.24:18። በተጨማሪም ትንቢተ አብድዩ ተመልከት። ከዚህ ጋር የሚከተሉትን ጥቅሶች አገናዝብ። ዘፍ.36:9፤ ዘኁል.20:18፤ ዘዐ.2:14፤ 23:7፤ መሳ.11:17፤ 1ኛ ነገሥ.11:1።

አማሌቃውያን የኤሳው ዝርያዎች ናቸው፤ ዘፍ.36:12፤ ዘዐ.17: 8-16፤ 1ኛ ሳሙ.15:3፤ 28:18፤ 2ኛ ሳሙ. 1:1፤ 1ኛ ዜና 4:43። ይህ ወገን በሲና ደቡብ ከሚገኘው ጅረት አንሥቶ የእስራኤል አገር ደቡባዊ ክፍል ዙርያ በያዘው ምድር የሚኖር ነበረ። የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ወጥቶ በጉዞ ላይ ሳሉ በመንገድ ጠብ አንሥቶበት በቃዴስ ተዋግቶት ነበር። እግዚአብሔርም በድርጊታቸው ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው አስቦ ተዋቸው፤ ዘፀ. 17:8-16። እነዚህ ወገኖች በመሳፍንት ዘመን እስራኤልን እጅግ ያስጨነቁትና ያስጠበቡት ስለ ነበረ በሳኦልና በዳዊት ዘመን እጥፍ ድርብ አድርጉ ተበቅሏቸዋል። በኋላም በንጉሥ ሕዝቅያስ ዘመን ዘራቸው በምድር እንዳይቀር ተደርጉ ተደምስሶአል፤ 1ኛ ሳሙ. 15:3፤ 28:18፤ 1ኛ ዜና 4:41-43።

ምድያማውያን አብርሃም ሣራ ከሞተች በኋላ ካገባት ከኬጡራ የወለዳቸው የምድያም ዝርያዎች ናቸው። እነዚህ ወገኖች ብዙውን ጊዜ ተዘዋዋሪ ስለነበሩ በዘላንነት የሚኖሩ ነበሩ። እነርሱም ዮሴፍን ለግብፃውያን ከሸጡት ከእስማኤላውያን ጋር የኖሩበትም ዘመን ነበረ።



ሙሴም ሚስት ያገባው ከእነዚህ ጐሣዎች ሲሆን ከእነርሱም ጋር ለ40 ዓመት ያህል ኖሮ ነበር። እነዚህ ወገኖች ከእስራኤላውያን ጋር ተስማምተው ሲኖሩ ሳለ አንዳንድ የጣዖት አምልኮን ነገር ስላስተማሯቸው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሙሴን የሚያጠፏቸውን ሠራዊት እንዲያሰልፍ ያዘዋል፤ ዘኁ. 31:1-3። እነርሱ ግን ከጥቂት ዘመናት በኋላ ኃይላቸውን አስተባብረው ከእስራኤል ጋር በመግጠም እስራኤላውያንን ያጠቋቸው ጀመር። ሆኖም ጌዴዎን በእግዚአብሔር ኃይልና ተአምራት ድል ሊያደርጋቸው ችሎአል፤ መሳ.7። በኋላ ግን ውለው አድረው ጠፍተዋል፤ ዘፍ.25:1-4፤ ዘጸ.2:16፤ ዘኁ.31:1-3።

ፍልስጥኤማውያን ከካም ነገድ የተወለዱ ጐሣዎች ሲሆኑ የሚኖሩት የከነዓንን ደቡባዊ ክፍል ይዞ በሚገኘው ምድር ነው፤ ዘፍ.10:14። በአብርሃም ዘመን ይኖሩ የነበሩት በዚሁ በእስራኤል ምድር ነበረ። እነዚህ ጐሣዎች በሳምሶን ዘመን እስራኤልን ሲያስጨንቁ የቆዩ ሲሆኑ በካህን ዔሊ ዘመን ደግሞ የዔሊን ልጆች ገድለው የእግዚአብሔርን ታቦት ማርከው ወደ አገራቸው ወሰደውት ነበር፤ መሳ.13:16። ከዚህ በኋላ 20 ዓመት ቆይተው በሳሙኤል ሠራዊት ተመትተው ድል ተደርገዋል። በሳኦል ዘመነ መንግሥት ግን እስራኤል ሊቋቋሟቸው የማይችሉ ከባድ ጦረኞች ሆነውባቸው ነበር። ዳዊትም የጭፍራ አለቃቸው የነበረውን ጐልያድን የገደለው በዚሁ ወቅት ነበረ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ሲዋጉ የኖሩ ጠንቀኛ ጠላቶቻቸው ነበር።

ፊንቄያውያን በቀድሞ ጊዜ ሲዶናውያን ተብለው ይጠሩ ነበር፤ የሐዋ.11:19፤ 15:3፤ 21:2። መኖሪያቸውም ከእስራኤል አገር በስተሰሜን በሚገኘው ምድር ነበር። ዋና ከተማዎቻቸውም ጢሮስና ሲዶና ይባላሉ። ፊንቄያውያን የኖኅ የበኲር ልጅ የሲዶን ዝርያዎች ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜም ሐማት በመባል ይታወቁ ነበረ። እነዚህ ወገኖች ሰላም ወዳድ የሆኑ የባሕር ላይ ነጋዴዎችን አርአያ እየተከተሉ ብዙ ነገር ቀስመዋል፤ በኋላም ሰሜናዊ አፍሪካን ይዘው ኃይለኛውን የካርቴጅ ሕብረት አቋቁመዋል። እነዚህ ወገኖች ለንግድ ሞያ አፍሪካን ሁሉ የዞሩ ከመሆናቸው በቀር ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በሠራ ጊዜ ለቤት ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን በማጓጓዝ ብዙ ረድተውት ነበር። አምላካቸውም ከሕዝብ አማልክት ሁሉ የከፋ በዓል የሚባል ጣዖት ነበረ። እንደ ሚስቱ ተደርጋ ትጠራ የነበረችውም እስራኤልን ያሳተችው የአካብ ሚስት የነበረችው ሲዶናዊቱ ኤልዛቤል ነበረች፤ 1ኛ ነገ.16:31።

ሶርያውያን ከከነዓን ሰሜናዊ ምዕራብ በሚገኝ ምድር የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። ዋና ከተማቸውም ደማስቆ ይባል ነበር። እነዚህ ወገኖች ከእስራኤል ጋር ብዙ ዘመን የተዋጉ ከመሆናቸው በቀር ሌሎች የእስራኤል ጠላቶች ማለት አሦራውያንና ባቢሎናውያን እስራኤልን በሚወጉዋት ጊዜ ረዳት ሆነው ያጠቋት ነበር፤ መሳ.10:6። በዳዊት ዘመነ መንግሥት ግን ዳዊትን ደኅና አድርገው አገልግለውታል። እነዚህ ሰዎች አብርሃም ከአጋር የወለደው የእስማኤል ዝርያዎች ሲሆኑ ዛሬም ሶሪያውያን እየተባሉ የሚጠሩት ናቸው።

<u>መሳፍንት</u>፡- የመሳፍንት ዘመን 1400-1100 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያጠቃልል ነው። በመጀመሪያው 300 ዓመታት ውስጥ እስራኤል በብዙ የአካባቢ ጠላቶች እጅ እየወደቀ ሲጨነቅ እግዚአብሔር ጩኸቱን ሰምቶ በመሳፍንት በኩል አርነት ሲያወጣው የቆየበት ዘመን ነው። እግዚአብሔር በዚህ ዘመን እስራኤል በመከራ ውስጥ እንድታልፍ የፈቀደው ንጉሡ ይሆናል የተባለውን ኢየሱስን ማምለክ ትታ የአሕዛብን አማልክት መከተል ስለወደደች ነው።

ኢያሱ ከሞተ ከጥቂት ዓመታት በኋላ እስራኤል እግዚአብሔርን ከማያውቁ አረማውያን ጋር በጋብቻ በመጣላለፍ ጣዖቶቻቸውንም ማምለክ ስለጀመሩ እግዚአብሔር የመስጴጦምያን ሕዝብ እስኪሥቶ ለ8 ዓመት ያህል እስራኤልን እንዲያስጨንቁ አድርጓል፤ መሳ.3፡5-7። ስለዚህ የመስጴጦምያ ንጉሥ ኩሰርሰቴም ተብሎ ይጠራ የነበረውን ምድር ገዛ፤ መሳ.3፡7-11። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የካሌብን የወንድም ልጅ ጐቶንያልን አስነሥቶ የመስጴጦምያን ንጉሥና ሕዝብ ከምድሪቱ በጦርነት አባዶ በማስወጣት እስራኤል ለ40 ዓመት በሰላም እንድትኖር አድርጓል።

ከ40 ዓመታት በኋላ እስራኤል እንደገና በእግዚአብሔር ላይ አመጽን ቀጠለች። በዚህ ጊዜ ደግሞ ሞአባውያንን አስነሥቶ ለ18 ዓመት እንዲያስጨንቋት በእጃቸው አሳልፎ ሰጥቷታል። ከዚህ በኋላ እስራኤል በእግዚአብሔር ፊት እያለቀሰች ምሕረትን በጠየቀች ጊዜ እግዚአብሔር የብንያምን ልጅ ናዖድን አስነሥቶ ከጠላቶችዋ እጅ ካዳናት በኋላ ለ40 ዓመት በነፃነት ኖራለች። መሳ.3፡12-30።

ሦስተኛው ወረራ የመጣባቸው ከከነዓናውያን ነበረ። እስራኤል ገና ወደ ከነዓን ምድር እንደ መጡ ከነዓናውያን በጦርነት አሠቃይተው ብዙ መከራ አድርሰውበት እንደነበረ ይታወቃል። አሁን ግን እስራኤል ራሳቸው በእነርሱ ኃጢአት ስለተጠመዱ እግዚአብሔር በስተ ሰሜን በኩል ባሉት እስራኤላውያን መካከል የሚኖሩትንና 900 ሠረገሎች የነበሩዋቸውን ከነዓናውያን አስነሥቶ ለ20 ዓመት እንዲወሩዋቸው አድርጓል።

ከዚህ በኋላ እንደልማዳቸው እስራኤል እንደገና ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ ጊዜ ዲቦራንና ባራቅን አስነሥቶላቸው ከጠላቶች እጅ እንዲድኑ አድርጐአል። እስራኤል ግን በጦርነቱ ወቅት በዛብሎንና በንፍታሌም የሚገኙትን ጽኑአን ኃያላንን ይዘው ከማጥቃታቸው በላይ የእግዚአብሔርም ኃይል ያግዛቸው ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሚገኙ አንዳንድ ታሪኮች እንደሚያስረዱን እግዚአብሔር ታላቅ አውሎ ነፋስን አስነሥቶ የከነዓናውያንን ፈረሶች ወደ ኋላ መለሳቸው። በዚያ ትልቅ ውጊያ ውስጥ የከነዓናውያን ፈረሰኞች እየሸሹ ከፊታቸው የነበረውን ወንዝ ለማቋረጥ ሲገቡ የፈረሶቻቸው እግር እየተያዘ በውኃው ውስጥ ሰጥመው አለቁ። እግዚአብሔርም በእንደዚህ ያለ መንገድ ለእስራኤል ድልን ሰጥቶታል፤ መሳ.5፡20-22።

ከምሥራቅ በኩል በምድያኖች የተወረሩት ወረራ አራተኛው ነበረ፤ አሁንም እስራኤል ከእግዚአብሔር ርቆ ጣዖት አምልኮውንና አመፃውን ማከናወን ስለቀጠለ ምድያን ለሰባት ዓመት እንዲያስጨንቋት አሳልፎ ሰጥቶታል፤ መሳ.5፡31። በዚህን ጊዜ እስራኤል ተጸጽቶ ምሕረት ከእግዚአብሔር በጠየቀ ጊዜ እንዲያድነው እግዚአብሔር ያስነሣው ሰው ከምናሴ ነገድ የሆነ ጌዴዎን የሚባል ነበረ። ጌዴዎን ምድያማውያንን ድል ለማድረግ ያቀደው የእስራኤልን ሕዝብ ለጦርነት በማሰለፍ ነበረ። ከብዙ ሺህ ሠራዊት ጋር በምንም ዓይነት የማይመጣጠኑትን 300 ሰዎች ብቻ እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ ለጦርነት አሰለፈ። እግዚአብሔርም በ300 ሰዎች ብቻ በመጠቀም ጠላቶቹን በፊቱ ስላንበረከከ ከዮርዳኖስ ማዶ ድረስ አሳዶ እንዲመታቸው አድርጓል፤ መሳ.6፡1-8፤32፤ መዝ.83፡9-11፤ ኢሳ.9፡10-26።



ከአሞናውያን ወገን የተነሣ ወረራ ጥቂት መሳፍንት እስራኤልን ካስተዳደሩት በኋላ መቶ ዓመት ያህል ቆይቶ ከእግዚአብሔር ርቆ የመኮብለል በሽታ አገረሸባቸው። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር ፍልስጥኤማውያንንና አሞራውያንን አስጨናቂ አድርጐ ሰደደባቸው። በእነዚህ ጠላቶቻቸው ከንድ ከዳሸቁ በኋላ እንደገና እግዚአብሔርን ለዕርዳታ ጠሩት። እርሱም ዮፍታሄን አስነሥቶ ከጠላቶቻቸው እጅ አድኗቸዋል፤ መሳ.10፡6-12፤ ዕብ.12፡32።

ከደቡባዊ ምሥራቅ ክፍል ከፍልስጥኤማውያን የተነሣባቸው ወረራ፤ መሳ.13፡1-16፡31። እስራኤላውያን አሁንም ደግመው በእግዚአብሔር ላይ አመፁ። በዚህን ጊዜ ለ40 ዓመት በፍልስጥኤማውያን እጅ ተረግጠውና ተደቁሰው እንዲገዙ ጣላቸው። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከመከራቸው ሊቤዣቸው ያቀደው በሳምሶን በኩል ነበር። በዚህን ጊዜ ሳምሶን ራሱ በኃጢአት ወድቆ ስለነበረ እግዚአብሔር እስራኤልን ሳያድናቸው ቀርቶአል።

ስለዚህ የእስራኤል ሥቃይ ይበልጥ እየከፋ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር ዔሊን አስነሥቶ ፈራጅ አደረገላቸው፤ 1ኛ ሳሙ.1፡1-9፡18።

በኋላም እግዚአብሔር በዔሊ ፋንታ ሳሙኤልን አስነሥቶ እስራኤልን ያስተዳድር ጀመር። ሳሙኤል በመሳፍንት ዘመን ከነበሩት አስተዳዳሪዎች መካከል ዋነኛው ሰው ሲሆን በአስተዳደሩም ነቀፋ ያልተገኘበት ቅን የእግዚአብሔር ሰው ነበረ።

ከእርሱ በኋላም እስራኤላውያን ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው በጠየቁት መሠረት እግዚአብሔርን አስፈቅዶ ሳኦልን አነገሣላቸዋል፤ 1ኛ ሳሙ.7፡3-12፤25። ከሳኦል በኋላም በእግዚአብሔር መሪነት ዳዊትን ቀብቶ አነገሣላቸዋል፤ 1ኛ ሳሙ.16፡11-14።

# ምዕራፍ 6

## የአሦራውያን መንግሥት

እግዚአብሔር እንደ ሀሳቡና እንደ እቅዱ በአንዱ መንግሥት መነሣትና በሌላው መንግሥት መውደቅ ውስጥ ያለውን አሠራር ለማወቅና ከዚህም ሌላ ለሰው ልጅ ደህንነት ያዘጋጀውን የመቤዠትን ሥራ ለመገንዘብ ስለ አሦር መንግሥት ማጥናት ይኖርብናል።

«የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል» ምሳሌ 21፡1።

## የአሦራውያን አነሣስ

ከዚህ ቀደም ብለን በምዕራፍ ሦስት ላይ ስለ አሦራውያን በተነጋገርነው ታሪክ ውስጥ አሦራውያን የሴም ልጅ የነበረው የአሹር ዝርያዎች እንደሆኑ ሰምተናል። እነዚህ ነገዶች በመጀመሪያ ጊዜ የሰፈሩት በባቢሎን ሲሆን በኋላ ግን የካም ልጅ በነበረው በንጉሥ ናምሩድ

ተባርረው በመውጣት በአሹር ስም ተሰይሞ አሦርያ በተባለው ሰሜናዊ ምድር መኖር ጀመሩ። አሦራውያን በመጀመሪያ በባቢሎናውያን ተገዝተው ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ቢሆኑም በኋላ ማለት እስራኤል ከግብፅ ነፃ በወጣችበት አካባቢ ራሰዋን የቻለች መንግሥት ሆናለች።

በዚያንም ዘመን የበላይነትን ስፍራ ለመያዝና ሌሎቹን ከቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ባቢሎን፥ አሶርና ግብፅ እርስ በርሳቸው ይፎካከሩ ነበር። በተለይ እስራኤል ለ40 ዓመታት ያህል በምድረ በዳ ትንከራተት በነበረችበት ዘመን የእነዚህ ሦስት አገር ጦር ሠራዊቶች ወደ ከነዓን በመመላለስ ከነዓናውያንን አዳከመዋቸው ነበረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእንደዚህ ዓይነተ መንገድ የምድሩን ሰዎች በጦርነት ሲያዳክም ቆይቶ በኋላ ምድሪቷን በቀላል ጦርነት እስራኤላውያን እንዲወርሱ አዘጋጀላቸው። እነዚህ በጦር ሠራዊቶች ከበባ ሕዝቡን ያዳከሙት ጦርነቶች አዳከመው የነበረው ከነዓናውያንን ብቻ ሳይሆን በከነዓን አከባቢ የነበሩትንም ጭምር ስለነበረ እስራኤል ከነዓንን ብቻ ሳይሆን የአካባቢዎቹንም ሕዝቦች ከቁጥጥርዋ ሥር እንድታደርግ ረድቷታል። ይህ ባይሆን ኖሮ እስራኤላውያን ሊቋቋሟቸው ስለማይችሉ በቀላሉ ድል በተደረጉም ነበር። ይህ ሁናቴ እግዚአብሔር ማንኛውንም አጋጣሚ ነገር በመጠቀም ሕዝቡን ከመጠበቅና ከማዳን ምን ጊዜም ወደ ኋላ ብሎ እንደማያውቅ ያስተምረናል።

እግዚአብሔር እስራኤልን ታላቅ ሕዝብ ለማድረግ ወጥኖ ስለነበር በሳኦል፥ በዳዊትና በሰለሞን ዘመን መንግሥት ተቀናቃኝ ጠላቶቻቸው የነበሩትን አሦር፥ ባቢሎንንና ግብፅን አዳከሞላቸው ነበር። ታሪክ እግዚአብሔር ግብፅን በመሰናዎች ካገኟቸው ንብረቶችዋና ከምትመካበት ኃይሏ ጋር አንደ ጠላት ይነግረናል።

አሦር በሰሜን አርሚንን፥ በምዕራብ ደግሞ ሄታውያንን፥ ኤላምንና ባቢሎንን አሸንፋ ድል አድርጋ ግዛቷንም ከፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጀምራ የኮአሽንና የኤላምን ተራራ ይዛ እስከ ሜዲትራኒያን ባሕር ድረስ አስፋፍታ ነበር፤ 2ኛ ነገ.15:24፤ 16:17፤ 1ኛ ዜና 5:6፤25፤ 2ኛ ዜና 28:20። ይህ አሶር የገነነችበት ዘመን በ1050 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አከባቢ ማለትም ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ ከመሾሙ ቀደም ሲል ነበረ። በኋላ ግን ሙላ አድራ አሶር ተዳክማ እጅግ አነስተኛ ሕዝብ ሆና ቀርታለች። እግዚአብሔር እነዚህ ሦስት አገሮችን ማለት ግብፅን፥ ሶርያንና ባቢሎንን እያመነመነ በማዳከም እስራኤል እየተባዛች ታላቅ ሕዝብ የምትሆንበትን መንገድ ቀደም ሲል ቀይሶ ስለነበረ ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ እስራኤል ጠገብ ስትልና በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ በምትጀምርበት ጊዜ እግዚአብሔር ከአመፃዋ ሊመልሳት አሶርን የመቅጫ ዱላ አድርጐ ለማስነሣት ከእስራኤል የበለጠች አድርጐ የሚያሳድጋት ጊዜ ነበረ።

በተለይ ከ255 ዓመት በኋላ ማለት ከ885-860 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ባሉት ዓመታት ውስጥ እስራኤላውያን ከአመፃቸው ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ባልሆኑ ጊዜ ዳግማዊ አሸር-ናስርፖል የተባለውን የአሦርን ንጉሥ አስነሥቶባቸው ከጤግሮስ ወንዝ እስከ ሜዲቴራንያን ባሕር ከዚያም እስከ ሊባኖስ ተራራ ድረስ ያለውን ምድር ሁሉ እንዲይዝና ሕዝቡንም ከቁጥጥሩ ሥር እንዲያውል አድርጐታል።

ከዚያም ከ860-826 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሣልሣዊ ሽልመኒዛር ንጉሥ ሆኖ በአሶርያ ላይ ነግሦ ነበር። ከአሶርያውያንም መካከል ብዙዎቹ አማልክታቸውን ማምለክ ትተው አንዱ እውነተኛ አምላክ ለማምለክ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰዋል። ይህም ጊዜ ዮናስ



ወደ አሦር ዋና ከተማ ወደ ነነዌ ሄዶ ንስሐ ባይገቡ እግዚአብሔር በሦስት ቀናት ውስጥ ከተማቸውን እንደሚገለባብጣት ባሳሰባቸው ጊዜና ሕዝቡ ሁሉ ከንጉሡ ጋር ማቅ ለብሰው ንስሐ በመግባት ወደ እግዚአብሔር የተመለሱበት ጊዜ ሊሆን ይችላል፤ ዮናስ 3:5-10።

በነነዌና በአጠቃላይ በአሦር የሚገኝ ሕዝብ ሁሉ አብዝቶ በእግዚአብሔር ላይ ሰላመጸ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ውሳኔ ላይ እስከመድረስ ድረስ አድርሶታል፤ ሉቃስ 11:30-32።

ሌላው የአሶር ንጉሥ ደግሞ ፑል ይባል ነበር። በዚያን ዘመን እስራኤል ከእግዚአብሔር ርቀው ወደ ሌሎች አማልክት ስለተመለሱ ዳዊት መኳንንቶችን፥ ሽማግሌዎችንና የአገሩን ታላላቆች ልኮባቸዋል፤ 2ኛ ነገ.15:18-20፤ 2ኛ ዜና 5:2።

በ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 17 ላይ እንደተወሳው በ730 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እስራኤል ወደ ኢየሩሳሌም እየተመለሱ በነበሩበት ዘመን የአሦርያው ንጉሥ ሽልመኒዘር ወደ ኢየሩሳሌም ከገቡት ከጥቂት አይሁዶች በስተቀር አብዛኛዎቻቸውን እስከ መጨረሻ ድረስ ምርኮኞች አድርጐ ወስዶአቸዋል።

# ምዕራፍ 7

## የእስራኤል መንግሥት

ስለ እስራኤል መንግሥት አነሳስና አወዳደቅ እንደዚሁም መንግሥታዊ እስራኤልና ይሁዳ ተብሎ ስለመከፈሉ ጉዳይ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ከመወሳቱ በስተቀር በ2ኛ ዜና 15:2 ላይ ደግሞ «እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ስትሆኑ እርሱ ከእናንተ ጋር ነው ብትፈልጉትም ይገኝላችኋል፤ ብትተዉት ግን ይተዋችኋል» ተብሎ ተነግሮአል።

እግዚአብሔር አምላክ እስራኤልን በበረታች ክንድ የተለያዩ ተአምራትንና ድንቆችን በመፈጸም በባርነትና በግዞት ከነበሩበት ከግብፅ ምድር አውጥቶ ለአባቶቻቸው ወደማለላቸው አገር ወደ ከነዓን አስገብቶአቸዋል። እነርሱ ግን እግዚአብሔር ንጉሣቸው ሳለ እንደ አሕዛብ በፊታችን የሚሄድ የሚታይ ንጉሥ ይንገሥልን ብለው ጌታን ናቁትና ተዉት። «እርሱም እንዳልነግሥባቸው ጠሉኝ» ብሎ ሳይቀስፋቸው ልመናቸውን ሰምቶ ሳኦልን ንጉሥ አድርጐ አንግሦላቸዋል። ሆኖም በላያቸው የነገሡት ብዙዎቹ ነገሥታት ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ከማቅረብ ይልቅ ከእግዚአብሔር መንገድ አርቀዋቸዋል።

እስራኤል ከግብፅ ወጥተው በከነዓን ምድር መኖር ከጀመሩ በኋላ በላያቸው ያነገሡአቸው ዋና ዋናዎቹ የመጀመሪያ ነገሥታት የሚከተሉት ናቸው:-

- ሳኦል:- ከ1095-1055 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለ40 ዓመታት፤
- ዳዊት:- ከ1055-1015 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለ40 ዓመታትና
- ሰለሞን:- ከ1015-975 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለ40 ዓመታት።

እስራኤላውያን በእነዚህ ነገሥታት አስተዳደር ሥር በነበሩበት ጊዜ ከጠንቀኛ ጠላቶቻቸው ማለት ከግብፅ፣ ከአሶርና ከባቢሎናውያን ጭቆና አርፈው ነበረ። ሆኖም አልፎ አልፎ መጠነኛ ችግሮች ይፈጥሩባቸው የነበሩት አንዳንድ ጥቃቅን የአካባቢው መንግሥታት ጨርሰው ጋብ አላሉላቸውም ነበር። እግዚአብሔር ግን ውሎ አድሮ እነዚህን ጥቃቅን ነገሥታት በዳዊት እጅ አሳልፎ በመስጠት ከቁጥጥሩ በታች እንዲውሉና እንዲገዙለት አድርጓል። እነዚህም መንግሥታት:- ፍልስጥኤማውያን፣ ከነዓናውያን፣ ሞአባውያን፣ አሞናውያን፣ አማሌቃውያንና ኤዶማውያን ናቸው። እስራኤልን በጣም የተጫኗቸውና የጎዷቸው የመስጴጦምያ ንጉሥ ርሽታይ ብቻ ቢሆንም እግዚአብሔር ከእርሱ እጅ እንኳ ቢሆንም በእጁ ብዙ ወራት ሳይቆዩ ፈጥኖ አድኖአቸዋል፤ መሳፍ.3፡9።

ዳዊት ከቀይ ባሕር አንሥቶ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ የነበረውን ግዛቱን ለልጁ ለሰለሞን አውርሶታል። ሰለሞንም ከግብፃውያን ጋር ተወዳጅቶ ስለነበር ፈረሶችንና ሠረገሎችን ከእነርሱ እየገዛ ለሒታውያንና ለሶርያውያን ይሸጥላቸው ነበር። ሰለሞን እግዚአብሔር የሰጠውን ሕግ በመጣስ ከከለዳውያንና ከአረማውያን ማለት ከጣዖት አምላኪ ሕዝብ ወገን ሚስቶችን አገባ። እነዚህ ሴቶችም ከእውነተኛው አምላክ ጎዳና አስናከሉት። ወደ ጣዖት አምላኪነትና አከባሪነት ወሰዱት። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰለሞንን መንግሥት አኩሌታ ከልጁ ከሮብዓም እጅ ቀድዶ ለሌላ ሰው ሰጠው፤ 1ኛ ነገ.11፡1-8። እግዚአብሔር ዳዊትን ከዘርህ ንጉሥ አይታጣም ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለት ስለነበረ ለሰለሞን ልጅ እግዚአብሔር ብንያምንና ይሁዳን ብቻ አስቀርቶለታል፤ 1ኛ ነገሥ.19፡9-13። የሰለሞን ብዙ ሚስቶች ከእግዚአብሔር እርግማንን አመጡበት እንጂ ምንም አልጠቀሙትም። በዚሁ ዓይነት መንገድ የዳዊት ሚስቶችም ለእግዚአብሔር ፈቃድ የቀና ልብ ስላልነበራቸው በቤተ መቅደስ ውስጥ ተሸሽጉ ካመለጠው ከትንሹ ልጅ ከዮአስ በስተቀር የዳዊት ዘሮች በሞላ ታርደው አልቀዋል። ያ ልጅ ከሞት ሊያመልጥ የቻለው እግዚአብሔር ዳዊትን ዘርህ ከምድር አይጠፋም ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለት ስለነበረ ነው፤ 1ኛ ነገሥ.11፡1-3፤ 2ኛ ዜና 22፡10-12።

እግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆቹን ከመታገሡ የተነሳ ወዲያውኑ ሳይቀጣቸው ቀርቶ የዘገየ እንደሆን ከኃጢአታቸው የተቀበላቸውና የሚያጸድቃቸው ስለሚመስላቸው ኃጢአት ማድረጋቸውን አቋርጠው ንስሐ በመግባት ፋንታ በኃጢአታቸው ይቀጥላሉ። ስለዚህ ማንም ሰው ንስሐ ሳይገባ በፊት እድናለሁ ብሎ ራሱን ሊያታልል አይገባም። ምክንያቱም ዳዊት እንኳ ንስሐ እስካልገባ ድረስ እግዚአብሔር እንዳልተቀበለው መመልከት ይቻላል፤ ዘዳ.17፡14-17፤ ዘኍል.32፡23።

## የእስራኤል መንግሥት ለሁለት መከፈል

ሰለሞን ከሞተ በኋላ ልጁ ሮብዓም የይሁዳ ንጉሥ ሆኖ ነገሠ። የቀረው አሥሩ ነገድ ግን ከሰለሞን ልጅ ከሮብአም ተለይቶ ኢዮርብዓም በሚባለው ንጉሥ ሥር ለመተዳደር የእስራኤል መንግሥት ሆኖ ተለየ፤ 1ኛ ነገሥ.11፡28-31። ይህም ማለት ከ12 ነገድ አሥሩ ሰሜናዊ መንግሥት ሲሆን ይሁዳና ብንያም ደግሞ ደቡባዊ መንግሥት ሆኖአል።

ሰሜናዊው መንግሥት ማለት እስራኤል ለ250 ዓመታት መንግሥቱ ጸንቶ ኖሮአል። በእነዚህም 250 ዓመታት ውስጥ ከነገሡት ነገሥታት መካከል 19ኙ እግዚአብሔርን



የማያውቁ ስለነበሩና ሕዝቡም ጣዖታትን ይከተል ስለነበረ ያለ እረፍት በዙሪያቸው በነበሩ ነገሥታት ይጠቁ ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ለዓለም በረከት እንዲሆኑ ለእስራኤላውያን ያንን 250 ዓመት ሰጥቷቸው ነበር። እነርሱ ግን አብዝተው አመፃቸውን ስለቀጠሉ በመጨረሻ ላይ በአሶርያውያን እጅ ምርኮኛ አድርጐ ሰጥቷቸዋል፤ 2ኛ ነገሥ.17።

በእስራኤል መንግሥት ውስጥ አራት ዋና ዋና የጣዖት አምልኮ የተካሄደባቸው ዘመናት ነበሩ። የመጀመሪያው ዘመን ኢዮርብአም በእስራኤል ላይ የነገሠበት ዘመን ሲሆን እርሱም በዚህ ዘመን እስራኤላውያን እንዲያመልኳቸው ሁለት የወርቅ ጥጃዎችን ሰጥቷቸዋል።

በሁለተኛው ዘመን ደግሞ አክዓብ በእስራኤል ላይ ገኖ የነበረ ታላቅ ንጉሥ ነበረ። በእርሱም ዘመነ መንግሥት ጣዖት እጅግ አብዝቶ በእስራኤል ይመለክ ነበር።

በዚህ በሦስተኛው ንጉሥ ዘመንም ጣዖት በእስራኤል አብዝቶ ይመለክ ስለነበረ ለጣዖቶቹ ካህናት ጭምር ይሠዉለት ነበር። በዚህ ዘመን የነበረው ኢዩ የተባለው ንጉሥ ግን የጣዖትንና የካህናቱን ዝክረ ነገር ከኢየሩሳሌም ጠረገ።

በአራተኛው ዘመን ደግሞ በእስራኤል ላይ ዋና ንጉሥ የነበረው ዳግማዊ ኢዮርብአም የተባለው ነበረ። በዚህን ጊዜ ኃጢአታቸው ተበራክቶ ሞትን እያፈራ ስለነበረ እግዚአብሔር አሶራውያንን አስነሥቶ ብዙዎቹን አስጨፍጭፎአቸዋል። ከእነርሱም ውስጥ ጥቂቶቹ በምድሪቱ ሊቀሩ የቀሩትን ወደ ሶርያ ማርከው ወስደዋቸው ነበር። በዚህን ጊዜ በምድሪቱ የቀሩት ጥቂት አይሁዳውያን ከአሕዛብ ጋር ተጋብተው ተካለሱ። አሁን በምርኮ ወደ ባቢሎን ተወስደው የነበሩት አይሁዶች ወደ አገራቸው ሊመለሱ እነዚህ ከአሕዛብ ጋር የተካለሱትን አይሁዶች ስለጠሉአቸው ራሳቸውን ከእነርሱ ገልለው ይኖሩ ጀመር። እነዚህ ከአሕዛብ ጋር የተካለሱት አይሁዶች በአዲስ ኪዳን ዘመን ሳምራውያን እየተባሉ የሚጠሩት ናቸው።

## የእስራኤል ነገሥታትና የነገሡበት ዘመናት ሠንጠረዥ

| ነገሥታት | የነገሡበት ዘመን | ነቢያት |
|---|---|---|
| 1. ቀዳማዊ ኢዮርብዓም | 28 ዓመት<br>1ኛ ነገሥ.11፡28-31ና<br>12፡13፤ 13፡1-22፤<br>33፡34። | አኪያ<br>1ኛ ነገሥ.14፡1-20 |
| 2. ናዳብ | 2 ዓመት<br>1ኛ ነገሥ.15፡25-28፤<br>15፡29-30 | |

| ነገሥታት | የነገሡበት ዘመን | ነቢያት |
|---|---|---|
| 3. ባኦስ | 24 ዓመት<br>1ኛ ነገሥ.15፡33 | ኢዩ<br>1ኛ ነገሥ.16፡1-17 |
| 4. ኤላ | 2 ዓመት<br>1ኛ ነገ.16፡6-8 | |
| 5. ዘምሪ | 7 ቀናት<br>1ኛ ነገሥ.16፡15 | |
| 6. ዘንበሪ | 12 ዓመት<br>1ኛ ነገሥ.16፡23-27 | ኤልያስ፥ ሚክያስ<br>1ኛ ነገሥ.22፡5-7 |
| 7. አክዓብ | 22 ዓመት<br>1ኛ ነገሥ.16፡28-29 | 2ኛ ዜና 18፡19፤<br>1ኛ ነገሥ.16 እና<br>2ኛ ነገ.2 |
| 8. አካዝያስ | 2 ዓመት<br>1ኛ ነገ.22፡40ና 51 | ኤልሣዕ<br>2ኛ ነገ. 2-8፤<br>13፡20-25 |
| 9. ኢዮራም | 12 ዓመት<br>2ኛ ነገሥ.3፡1 | ኤልሣዕ |
| 10. ኢዩ | 28 ዓመት<br>2ኛ ነገ.9፡1-3፤ 10፡36 | ኤልሣዕ |
| 11. ኢዮአካዝ | 17 ዓመት<br>2ኛ ነገ.13፡1 | ኤልሣዕ |
| 12. ዮአስ | 16 ዓመት<br>2ኛ ነገ.13፡9፤ 14-19 | ዮናስ |
| 13. ኢዮርብዓም | 41 ዓመት<br>2ኛ ነገ.14፡16-23ና 29 | አሞጽ |



| | | |
|---|---|---|
| 14. ዘካሪያስ | 6 ወር<br>2ኛ ነገ.14፡29፤ 15፡8-12 | |
| 15. ሰሎም | 1 ወር<br>2ኛ ነገ.15፡13-15 | |
| 16. ምናሔ | 10 ዓመት<br>2ኛ ነገ. 15፡16-22 | |
| 17. ፋቂስያስ | 2 ዓመት<br>2ኛ ነገ.15፡23-26 | |
| 18. ፋቂሔ | 20 ዓመት<br>2ኛ ነገ.15፡27-31 | አቢድ |
| 19. ሆሴዕ | 2 ዓመት<br>2ኛ ነገ.15፡30 | ኢሳይያስና<br>ሚክያስ |

እስራኤል ልባቸው ከአምላካቸው ርቆ በሰዎችና በአማልክት ለመታመን ቢሞክሩም እንደ እርሱ ሊሆኑላቸው አልቻሉም። በዚያን ጊዜም ረድኤትን ክሰው እንጂ ከእግዚአብሔር አልፈለጉም፤ 2ኛ ነገ.15፡19፤ 17፡4፤ ሆሴዕ 5፡13፤ 7፡8-11፤ 8፡9-10፤ 13። በዚህም ምክንያት በምድሩ ሁሉ ጣዖት ነበረ። ከዚህ በቀር ሕዝቡ በአመፀኝነትና በነፍስ ግድያ ተግባር ተሰማሩ፤ ሆሴዕ 4፡12-14፤ 10፡12-13። ሲያጠፉአቸው ወደ ነበሩት ወደ ከነዓናውያን ተመልሰው ክፉ ሥራቸውን ተማሩ፤ ሆሴዕ 12፡7-8። እነርሱም ልክ እንደ እነርሱ በከንፈራቸው እንጂ ከልባቸው ንስሐ መግባትን ተዉ፤ ሆሴዕ.5፡4፤ 12፡8፤ 7፡16። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔርንና ቃሉን ረስተው ነበር፤ ሆሴዕ 4፡1-18።

## የይሁዳ መንግሥት

የእስራኤል ነገሥታት 250 ዓመት ብቻ የነገሡ ሲሆን የይሁዳ ነገሥታት ግን ለ400 ዓመት ያህል ከዳዊት ዘር በነበሩ በ19 ነገሥታት ተዳድራ ነበር።

የነበረውን ኤዶምን በሽፍትነት አስነሥቶ እንዲያስጨንቀው ከማድረጉ በላይ ዓረቦችና ፍልስጥኤማውያን ኢየሩሳሌምን እንዲወሩ አድርጓል። ከዚያም በኋላ በነቢዩ በኤልያስ በኩል እግዚአብሔር ከባድ የሆነ የሆድ በሽታ እንደሚያደርስበትና እርሱም በዚህ በሽታ ጠንቅ እንደሚሞት በጽሑፍ አድርጎ አሳውቆታል። እርሱም ልክ በነቢዩ እንደተነገረው በከባድ የሆድ በሽታ ተሰቃይቶ ሲሞት የቀሩት ልጆቹ ተገድለው ለዘር አንድ ልጅ ብቻ ቀርቶት ነበር፤ 2ኛ ዜና 21፤ 22፡10-12፤ 2ኛ ነገሥ.11፡1-3።

6. አካዝያስ፡- አካዝያስ መጥፎ ንግሥት ከነበረችው ከኤልዛቤል የልጅ ልጅ ከጎቶልያ የተወለደ ሰው ነበር። የዳዊት ቤተሰብ እጅግ በጣም አጸያፊ የነበረ የጣዖት አምልኮ ያካሂዱ ከነበሩት ከኤልዛቤልና ከአክዓብ ቤተሰብ ጋር በጋብቻ ስለተጣመሩ የዳዊትን ቤት እስከ አሁን ድረስ የእግዚአብሔር ፍርድ እየተከተለው ነበር። የአካዝያስ እናት ልጅዋን ከእግዚአብሔር የሚያርቀውን ርካሽ የሆነ የጣዖት አምልኮንና ክፋትን ታስተምረው ነበር። በኋላም የእስራኤልን ንጉሥ ኢዮራምን ለማገዝ ከሦርያውያን ጋር ሲዋጋ ቆይቶ ኢዮራም ስለቆሰለ ጦርነቱን አቋርጦ ቁስሉን ሊታከም የሄደውን የአክዓብን ልጅ ኢዮራምን ለማየት ወደ ኢይዝራኤል ወረደ። እግዚአብሔር በዚህ ተቆጥቶ የአክዓብን ቤት እንዲያጠፋ ባስነሣው በኢዩ እጅ ተገደለ። በዚህን ጊዜ እናቱ ጎቶልያ የልጅ ልጆችዋን ገድላ በፋንታው ነገሠች። እርስዋም በይሁዳ ላይ በነገሠችበት ዘመን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አስፈርሳ የበዓልን የማምለኪያ ቤት ሠራች። እግዚአብሔርን የሚያመልኩትንም አንዳንድ ሰዎች አስገደለች። በኋላም ከአካዝያስ ልጆች መካከል ሸሽገው ያሳደጉትን ኢዮአስን በሥፍራዋ ካነገሡ በኋላ እርስዋን ገደሉአት፤ 2ኛ ዜና 22፡10-23፡15።

7. ኢዮአስ፡- ኢዮአስም ከወንድሞቹ መካከል ከሞት ተርፎ የይሁዳ ንጉሥ መሆን ችሎአል። እነሆ ከዳዊት ወገኖች ለዘር የቀረ ሰው እርሱ ብቻ ነበረ። እርሱም በይሁዳ ላይ በነገሠ ጊዜ ገና የሰባት ዓመት ብላቴና ስለነበረ ካህን የነበረው አጎቱ በሞግዚትነት ያስተዳድርለት ነበረ። ኢዮአስ በአጎቱ ሞግዚትነት እያስተዳደረ በነበረበት ወቅት አጎቱ የጣዖትን ዘር ሁሉ ከይሁዳ አስወገደ። በኋላም አጎቱ ሲሞት እርሱ እያስተዳደረ ሳለ የአጎቱ ልጅ የቤተ መቅደሱን ካህን ስለገደለ እግዚአብሔር ተቆጥቶ አሦራውያንን በይሁዳ ላይ አስነሥቶ በዚያ ጦርነት ውስጥ ኢዮአስ በገዛ አሽከሮቹ ተገድሎ ሞቶአል፤ 2ኛ ዜና 24፡24-25፤ 2ኛ ነገሥ.11፡12፤ 2ኛ ዜና 22፡10-24፡27።

8. አሜስያስ፡- ከአባቱ በኋላም የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ ነገሠ። እርሱም በእግዚአብሔር ታምኖ ጠላቶቹን ካሸነፈ በኋላ ከጠላት አገር የተማረኩትን ጣዖታት ማምለክ ጀመረ። እግዚአብሔርም የእስራኤልን ንጉሥ አስነሥቶ ከተማውን ካዘረፈው በኋላ እርሱንም አሳዶ አስገደለው።

9. ዖዝያን፡- ዖዝያን በእግዚአብሔር የተወደደና በፊቱም ቅን የነበረ ሰው ከመሆኑ በላይ በጦርነትም ታላቅ ጀብደኛና ጀግና የሆነ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ባቃናለትና ከፍ ከፍ ባደረገው ጊዜ ልቡ ለጥፋት ታበየ። እርሱም ያልተፈቀደለትን ለሌዋውያን ብቻ የተሰጠውን የቤተ መቅደስን አገልግሎት ሥራ ለመሥራት ዕጣን ማጠን ጀመረ። በዚህን ጊዜ በእግዚአብሔር ተቀስፎ በለምጽ በሽታ ተመታና በውርደት ሞት፤ አሞጽ 1፡1፤ ዘካ.14፡5፤ 2ኛ ዜና 26።



10. ኢዮአታም፡- በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተወደደ ተግባር ፈጽሞ ስለነበር ጠላቱን ድል በማድረግና በብልጽግና ባረከው። ኋላም ከአባቶቹ ጋር ተከማቸ።

11. አካዝ፡- አካዝ መጥፎ ንጉሥ ነበረ። በደሉም የይሁዳ ሕዝቦች ሞሎክ የተባለውን ጣዖት እንዲያመልኩ ማድረጉ ነው። ከዚህም በቀር ልጆቹን እንኳ ለሞሎክ መሥዋዕት አድርጎ ያቀርብ ነበር። በኋላም አመጹ እየጨመረ ስለሄደ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሰዎች እንዳያመልኩት ቤተ መቅደሱን አዘግቶአል። በመጨረሻም እግዚአብሔር አሦርን አስነሥቶ ብዙ ሕዝብ እንዲፈጁ ካደረገ በኋላ ታላቅ ምርኮንም ወደ ደማስቆ አግዘዋል። የእስራኤል ሠራዊትም ይሁዳን መትተው የእርሱ ግዛት የነበረውን የፍልስጥኤማውያንን ምድር ወስደውበታል። በእርሱ እርኩሰት የተነሣ ይሁዳ ራስዋ እጅግ ተዋረደች፤ 2ኛ ዜና 28።

12. ሕዝቅያስ፡- ሕዝቅያስ ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ በሚበልጥ እግዚአብሔርን በቅንነት የተከተል መልካም ሰው ነበር። እርሱም አስቀድሞ የጣዖትን አምልኮ በጠቅላላው ከይሁዳ ምድር ካስወገደ በኋላ ተዘግቶ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በማስከፈት አይሁድ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው እግዚአብሔርን ማምለካቸውን እንዲጀምሩ አድርጓል። ከዚህም በስተቀር ከሰለሞን ዘመን ጀምሮ የፋሲካ በዓል መከበሩ ተጓጉሎ ስለነበረ እንደገና ይህ በዓል እንዲከበር አድርጓል። ሕዝቅያስ ይህን ሁሉ ሲያደርግ በእግዚአብሔር ታምኖ ስለነበረ እግዚአብሔርም በነገር ሁሉ ከእርሱ ጋር ነበረ። ስለዚህም ሥራውን ሁሉ አከናውኖለታል። ሕዝቅያስ በነገሠ በስድስተኛው ዓመቱ ሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ወደቀ። ሰናክሬም የተባለው የአሦር ንጉሥ ይሁዳን ባስወረረ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ስለይሁዳ ተዋግቶ ድል አድርጓቸዋል። ከዚያም በኋላ ሕዝቅያስ እስከሞት በሚያደርስ በሽታ ታሞ ሳለ እግዚአብሔር በዕድሜው ላይ ሌላ 15 ዓመት በመጨመር ጸሎቱን መልሶለታል። ሆኖም ሕዝቅያስ በነዚያ 15 ዓመታት ውስጥ በይሁዳ ውስጥ ካሁን ቀደም ያልነበረ ዓይነት ምናሴ የሚባል ክፉ ልጅ ሊወልድ ችሎአል። ይህ ንጉሥ ለይሁዳ እንደ መቅሰፍት ተደርጎ የተሰጣት ነበረ። ስለዚህ ሕዝቅያስ 15 ዓመት ዕድሜ ሲያገኝ መኖሩ ለሕዝቡ ጥቅም ወይም ለእግዚአብሔር ክብር ይሆን እንደሆነ አልጠየቀም። ስለዚህ ሕዝቅያስ ተጨማሪ ዕድሜ ባይጠይቅ ኖሮ ይህ ክፉ ንጉሥ ባልተወለደ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ለኛ በጐ የሆነውን ነገር ስለሚያውቅ ሁልጊዜ የእርሱን ፈቃድ መሻት ለእኛም ሆነ ለሕዝባችን ፈውስና ጠቃሚ ይሆናል። የእግዚአብሔር መንገድ ሁልጊዜ የተሻለና የሚመረጥ ነው፤ መዝ.106፡152፤ 2ኛ ዜና 29፡32፤ 2ኛ ነገ.18-20።

13. ምናሴ፡- ምናሴ በይሁዳ ከነገሡት ነገሥታት ሁሉ በላይ የከፋ ነበረ። የይሁዳ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ርቆ ጣዖትን እንዲያመልክ ቀስቃሽና አነቃቂ ሆነ። እርሱም ጣዖትን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በመትከል ቤተ መቅደሱን አረከሰ። ከዚህም ሌላ ላቆማቸው ጣዖታት በመስገድ ልጆቹን ሳይቀር እያረደ በእሳት በማሳለፍ መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባቸው ነበር። ከዚህም በቀር ምናሴ ከእርኩሳን መናፍስት ጋር በመወዳጀቱ የሚያስፈልገውን ነገር ከእግዚአብሔር በመጠየቅ ፋንታ አማካሪዎቹ ርኩሳን መናፍስት ስለነበሩ እነርሱን ይጠይቅ ነበር፤ 2ኛ ዜና 33፡1-9። በኋላም በአይሁድ ታሪክ ውስጥ እንደተጻፈው የምናሴ ድርጊት እጅግ መጥፎ መሆኑን ይነግረው የነበረውን ነቢዩን ኢሳይያስን አርዶታል። እግዚአብሔርም ለድርጊቱ በቀልን እንዲያመጣበት ሶርያውያንን አስነሥቶ በምርኮ በሰንሰለት ታስሮ ተወሰደ። እርሱም በመከራው ዘመን

ወደ እግዚአብሔር ጮሆ በማልቀስ ንስሐ ስለገባ በሌላ ዘመን መልሶ ወደ አገሩ እንዲገባ አድርጎታል። ከዚህ በኋላ ምናሴ እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ስላወቀ ሌሎችን አማልክት ሁሉ አስወግዶ እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ ጀመረ፤ 2ኛ ዜና 33፡1-20፤ 2ኛ ነገሥ.21፡1-18።

14. አሞጽ፡- አሞጽም የአባቱን መንገድ ተከትሎ ከእግዚአብሔር በመራቅ ጣዖትን ማምለክ ስለመረጠ እግዚአብሔር ቶሎ ብሎ ቀሰፈው። አባቱ ምናሴ ጣዖትን ሙልጭ አድርጎ ከሀገሪቷ ማስወገድ እስከማይቻል ድረስ ምድሪቷን አብክሎአት ስለነበረ ልጁ እርሱን ተከትሎ በስሕተት መንገድ መራመድን አላደረገውም። ስለዚህ አሞጽ በገዛ አሽከሮቹ በቤቱ ውስጥ ታርዶ ሊሞት ችሎአል፤ 2ኛ ዜና 33፡21-25፤ 2ኛ ነገሥ.21፡19-24።

15. ኢዮስያስ፡- ኢዮስያስ በዘመኑ የተወደደና እግዚአብሔርን ለማገልገል ቅን ልብ የነበረው ንጉሥ ነበረ። እርሱም በተቻለው መጠን ጣዖታትን ሁሉ ከይሁዳ አስወግዶ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ንስሐ እንዲገባ የጣረ ሰው ነው። ከዕለታት አንድ ቀን በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሕጉ መጽሐፍ መገኘቱን ሰምቶ አስመጥቶ ሲያስነብበው በይሁዳ ላይ ሊመጣ ያለውን መቅሰፍት ሰምቶ ልብሱን በኃዘን ቀድዶ ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ኢዮስያስ እግዚአብሔርን ለማገልገል በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት ቃል ኪዳኑን አደሰ። ሕዝቡ ምናሴ ለ50 ዓመት በይሁዳ በነገሠበት ዘመን ልቡ በጣዖት አምልኮ ብዙ ስለተወሰደ ለጊዜው ለይስሙላ ያህል ንስሐ ቢገባም ተመልሶ ወደ ጣዖት አምልኮው ሄዶአል። ኢዮስያስ በነገሠበት ዘመን ዳንኤል ገና ትንሽ ብላቴና ነበር። ከዚህ በኋላ አሶር በግብፃውያን በተወረረችበት ዘመን ኢዮስያስ የአሶር ረዳት ሆኖ በጦርነቱ ላይ እየተዋጋ ሳለ ተገደለ። ኢዮስያስ ዓላማውን ትቶ ከእግዚአብሔር አመራር ስላፈነገጠ ለይሁዳ መቀጣጫና ማስጠንቀቂያ እንዲሆን አድርጎታል። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ለጥቂት ዘመን ቁጣው በይሁዳ ላይ እንዳይደርስ አስቀርቶአል፤ 2ኛ ዜና 24፡35፤ 2ኛ ነገ.22፡23-30።

16. ኢዮአክስ፡- ኢዮአክስ በእግዚአብሔር ፊት ክፉና አጸያፊ የሆነ ድርጊት በመፈጸሙ እግዚአብሔር መንግሥቱ በወንድሙ እንዲወሰድ አድርጎ እርሱ በግብፃውያን ተሸንፎ በምርኮ እንዲወሰድ አድርጎታል። በስፍራው የነገሠው ወንድሙ ኤልያቄም ይባላል፤ 2ኛ ዜና 26፡1-4፤ 2ኛ ነገ.23፡31-33።

17. ኤልያቄም፡- ኤልያቄም በእግዚአብሔር ፊት መጥፎ ንጉሥ ሰለነበረ ከ3 ዓመት በኋላ ናቡከደነፆር በሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢሎን ወስዶታል። ከዚያም ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ የባቢሎን መንግሥት ወኪል በመሆን አገልግሎት መስጠት ጀመረ። ውሎ አድሮ ግን በባቢሎን መንግሥት ላይ አመፅን በመጠንሰስ ግብፅን ግብረ አበሩ በማድረግ የባቢሎን ጠላት ሆነ። በዚህን ጊዜ ነቢዩ ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከበትን መልእክት ደጋግሞ ሰላስታወቀው በጥላቻ ዓይን ስለሚመለከተው ሊገድለው ይፈልግ ነበር። ኤልያቄም አሻፈረኝ ብሎ በአመፁ በቀጠለ ጊዜ እግዚአብሔር የከለዳውያንን፥ የአሶራውያንን፥ የአሞንና የሞአባውያንን ሠራዊት አስነሣበት፤ 2ኛ ዜና 36፡5-8፤ 2ኛ ነገ.23፡34።

18. ዮአኪን፡- በእግዚአብሔር ፊት ነውረኛና አስከፊ ድርጊትን ሰለፈጸመ እግዚአብሔር በባቢሎናውያን እጅ አላልፎ በመስጠት እንዲማረክ አድርጎታል፤ 2ኛ ዜና 36፡9-10፤ 2ኛ ነገሥ. 24፡6-17፤ 25፡27-30።



19. ሴዴቅያስ፡- የኢዮራም ወንድም በባቢሎናውያን መንግሥት ሥልጣን በይሁዳ ላይ እንዲነግሥ ተደረገ። ሴዴቅያስ ከመተላለፉና ከጣዖት አምልኮው ከነሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ በኩል ደጋግሞ ቢያስጠነቅቀውም እምቢ አለ። ሕዝቡም ይባስ ብለው በቃሉና በነቢያቱ ላይ ማላገጥና መሳለቅ ጀመሩ። በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ስላለቀ የባቢሎንን ንጉሥ አስነሥቶ ሕዝቡን በሰይፍ አስጨፈጨፈው፤ አንዳንድ ከሰይፍ ያመለጡትንም የባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን ተማርከው በመወሰድ በዚያ ለ70 ዓመት ተገዙ። ሴዴቅያስም በባቢሎን ንጉሥ ከተያዘ በኋላ ልጆቹ በፊቱ እንዲታረዱ ተደርገው እርሱንም ዓይኖቹን ጐልጉለው ካወጡት በኋላ በሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን ከወሰዱት በኋላ በዚያው በባቢሎን ሞተ፤ 2ኛ ዜና 36፡11-21፤ 2ኛ ነገሥ.24፡17-26። ሴዴቅያስ ከዳዊት ዘር ግንድ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከይሁዳ ቤተሰብ የመጨረሻው ንጉሥ ነበረ። በዘመናት መደምደሚያ ላይ ግን የይሁዳ አንበሳ የሆነው ክርስቶስ ከዳዊት ቤት ተነሥቶ በምድር ላይ ለሺህ ዓመት ይነግሣል። ይህ ከመሆኑ በፊት ከካቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ድረስ ያለው ዘመን የአሕዛብ ዘመን ይባላል፤ ሉቃ. 2፡24። በዚህ በአሕዛብ ዘመን አይሁድ አብዛኛውን ጊዜ በዓለም ተበትነው የራሳቸው መንግሥት ስለማይኖራቸው ነው።

# ምዕራፍ ስምንት

## ሁለተኛ የአሦራውያን ዘመነ መንግሥት

እስራኤል እግዚአብሔርን ትተው ጣዖትን ስላመለኩ አሦራውያንን የመግረፍያ ጨንገር አድርጎ አስነሥቶባቸዋል። በትንቢተ ኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፡- «አሦርያ የቁጣዬ በትር ነው። የመቅሰፍቴም ጨንገር በእጆቹ ነው» ኢሳ.10፡5፤14። አሦር እግዚአብሔርን ባታውቅና ፈቃዱንም ለማድረግ ግድ የለሽ ብትሆንም ቅሉ እግዚአብሔር ይሁዳን ለመበዝበዝና ንብረትዋን ሁሉ ለምርኮ ለመስጠት የቁጣው ዱላ አድርጎ ተጠቅሞባታል።

ሁለተኛው የአሦር ዘመነ መንግሥት አስተዳደር 4ኛው ትግለትጵላዘር በተባለው ንጉሥ በ745 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ገደማ ተጀመረ። እርሱም ምዕራብ አሦርን በሙሉ አንድ አድርጎ ለመግዛት የሞከረ በጣም ጨካኝና ድል አድራጊ ንጉሥ ነበረ። ይህ ንጉሥ ምዕራብ አሦርን በጠቅላላ አንድ ሕዝብ እንዲሆን የተጠቀመው ዘዴ በተለያዩ ስፍራ ይኖሩ የነበሩትን የአሦር ጐሳዎች በተወሰነ ቦታ እንዲኖሩ በማሰባሰብ ነው። በዚህ ዓይነት ዘዴ ሕዝቡን ሁሉ አንድ ለማድረግ ተሰፋ አድርጎ ነበር።

የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ፋቁሔ በጌታ ላይ ክፉ ሰላደረገ ከነዓን በጠላት ተወራ ሕዝብዋ ሁሉ ከዮርዳኖስ ማዶ ከሚኖር ሕዝብ ጋር ተማርኳል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር የይሁዳ ንጉሥ የነበረውን አካብን ቢያስጠነቅቀውም ከአሦር ንጉሥ ከትግላትጵላዘር ጋር አንድ ግንባር ፈጥሮ በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ፥ በደማስቆ ንጉሥ በረአሶን ላይ አድሞባቸዋል። አይሁድ

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ከአሕዛብ መንግሥት ጋር በመወዳጀት በሕዝበ እስራኤል ላይ ስለተነሣችባቸው እግዚአብሔር በዚህ ተቆጥቶ ይሁዳ የእስራኤል ገባሬ እንድትሆን አድርጓታል፤ ኢሳ. 7። ትንሽ ቆይቶም ወዳጅዋ የነበረው አሦር ተመልሶ ጠላት ሆነባትና ጦር ሠራዊቱን ልኮ አስደበደባት። በዚህም ዘመን ቀዳማዊ ስል መናሦር በ722 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የእስራኤልን ንጉሥ አሸነፈ።

ሆሴዕ አልገብርም ብሎ ከግብፅ ንጉሥ ጋር በውስታ አንድ ግንባር ፈጥሮ እስራኤልን ወረራት። በዚህም ጦርነት ሳብያ ብዙ የሰማርያ፥ የፋርስና የእስራኤል ሕዝቦች ተገድለው የቀሩት ደግሞ ወደ አሦርና ወደ ባቢሎን ተወስደው በባርነት ተሸጠዋል። እስራኤልም ለመጨረሻ ጊዜ መንግሥት አልባ ሕዝብ ሆና የተበተነችው በዚህን ጊዜ ነው፤ ሕዝ.42። በዚህ ጦርነት ሳቢያ ካለቁት ብዙ አይሁዳውያን መካከል በምድሪቱዋ የቀሩት ጥቂት አይሁዳውያን በመካከላቸው ከሚኖሩ አሕዛብ ጋር በመጋባት ተከላለሱ። ውሎ አድሮም እነዚህ የአይሁድ ክልሶች ሳምራውያን ተብለው ይጠሩ ጀመር። ከዚያም ይሁዳ በአሦር ንጉሥ በሰናክሬም ተወረረች።

የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስ በነገሠ በ14ኛው ዓመት አሦርያውያን ይሁዳን ወረሯት፤ 2ኛ ነገ.18፡13። የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስም እግዚአብሔር በአሦርያውያን ላይ ድል እንዲሰጠውና ዓለም መላዋ እርሱ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ታውቅ ዘንድ እጥብቆ ጸለየ። እግዚአብሔር የሕዝቅያስን ጸሎት ሰምቶ መልአኩን ልኮ በአንድ ምሽት 185 ሺህ አሦራውያንን ካስገደለ በኋላ የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ወደ ዋና ከተማው ወደ ነነዌ እንዲመለስ አድርጐታል፤ ኢሳ.37፡16-20። እርሱም ወደ ከተማው እንደተመለሰ በፊት በአሦራውያን ወታደሮች ቁጥጥር ሥር በመዋል ተሸንፎ የነበረው የባቢሎን ሠራዊት እንደገና በማመጽ ከተማውን አቃጠለበት። በኋላም በ681 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በገዛ ራሱ ልጆች እጅ ተገድሎ ሞተ።

ከእርሱ በኋላ የነገሠው ንጉሥ አዛርሐዳንም ባቢሎንን መልሶ ካደሰ በኋላ በፋርስና በፋርስ ባሕረሰላጤ አካባቢ እስከ ቆጵሮስ ድረስ ያለውን ምድርና እንዲሁም ግብፅን ጨምሮ እንደያዘ በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ ተነግሮአል፤ ኢሳ.19፡4። ከዚያም ጥቂት ዘመን ቆይቶ የይሁዳ ሕዝብና የይሁዳ ሕዝብ መሪ የነበረው ንጉሥ ምናሴን ማርኮ ወደ ይሁዳ ወስዶአቸዋል።

እግዚአብሔር ሌላ ታላቅ ሕዝብ አስነሥቶ የእስራኤል ደንበኛ ጠላት የነበረውን አሦርን በታላቅ ጭካኔ እንዲመታ አድርጐታል። በዚህን ጊዜ ግብፅና ባቢሎን ራሳቸውን የቻሉ ነፃ አገሮች ሆነው ስለነበር ኃይላቸውን በአንድ ላይ በማጣመር ነነዌን የፍርስራሽ ክምር እስክትሆን ድረስ አፈራርሰው አቃጥለዋታል። ከዚያም ናሆም በትንቢቱ እንደተናገረው የቄዳር ወንዝ ሞልቶ የከተማውን ቅጥር አፈራርሶ እንደገባ ሁሉ ጠላቶቻቸውም ወደ ከተማው ገብተው ከተማውን የፍርስራሽ ክምር አድርገውታል፤ ናሆም 2፡6-9። ንጉሡም ሚስቶቹንና አሽከሮቹን እንዲሁም ብርና ወርቁን በቤተ መንግሥቱና በቤተ መቅደሱ ውስጥ እንዳከማቻቸው በእሳት ጋይተው አለቁ። እርሱም በወላፈኑ ነዶ ጠፋ፤ ናሆም 3፡14-15። ወገኖቹ የነበሩት አሦራውያን ክፉና ጨካኝ ስለነበረ በመጥፋቱ ደስ አላቸው፤ ናሆም 3፡19። አሦር በጣም አመፀኛ ሕዝብ በመሆኑ እግዚአብሔር ፈጥኖ ባጠፋው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ወገን የሌላ ክፉ ሕዝብ መቅጫ መሣሪያ አድርጐ ይጠቀምበት ጀመር።



ሕዝቄልና ሌሎች ነቢያት ስለ አሦርያ አመፀኛነት የተነበዩትን ቃል በሕዝ.23፡12-15፤ በኤር.12፡18-19 እንዲሁም በናሆም 3፡4 ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ይቻላል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ሁለተኛው የባቢሎን መንግሥት አስተዳደር

## 606-538 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት

### ዳንኤል 2፡37-38

እስራኤል እግዚአብሔርን በተወች ጊዜ ጌታ አሦራውያንን አስነሥቶ ብዙ መከራና ሞት በማድረስ የቀሩትን ለምርኮ እንደ ሰጠ ሁሉ ይሁዳም ጐረቤትዋን አይታ አመፅ ከማድረግ ስላልተቆጠበች ከ150 ዓመት በኋላ የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን አስነሥቶ ተመሳሳይ ቅጣትና ምርኮኛነት እንዲፈጸምባት አድርጓል። ከዚህም በቀር የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር የግብፅን ንጉሥ ፈርዖን ኒካኡን በኤፍራጥስ ምድር ከርከሚሽ በተባለው ሥፍራ አሸንፎት ከእስያ ምድር ለቆ እንዲጠፋ አድርጐታል። ስለ ፈርዖን ኒካኡ የተጻፈ ታሪክ በ2ኛ ነገሥ. 23፡31-32፤ 2ኛ ዜና 35፡20 ይገኛል። እንግዲህ ናቡከደናፆር በኢየሩሳሌም ላይ ዘምቶ የቻለውን ያህል ሕዝብ በጦርነት ካጠፋ በኋላ የከተማዋን ንብረትና የቀሩትን ሰዎች ወደ ባቢሎን የማረከው የግብፅን ንጉሥ ፈርዖን ኒካኡን ከእስያ ምድር ካባረረ በኋላ ነው። እርሱም ለመጀመሪያ ጊዜ የኢየሩሳሌምን ከተማ ወሮ ሕዝቧን ወደ ባቢሎን ምድር ማርኮ ያፈለሰው በ606 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበረ።

ከተማራኪዎቹም መካከል ዳንኤልና ሦስቱ ወዳጆቹ ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጐም ይገኙባቸው ነበረ፤ ዳን. 1፡6-7። ከዚህም በኋላ 8 ዓመት ቆይቶ ናቡከደነፆር በ598 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ለሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ ንጉሡን ኢዮአቄምንና ሌሎች ብዙ ሰዎችን ወደ ባቢሎን ማርኮ ወሰዳቸው። አሁንም ሌላ 9 ዓመት ከቆየ በኋላ በ589 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ዘምቶ ከተማዋን ጨርሶ ካፈራረሰ በኋላ በ587 ብዙዎቹን ሰዎች ገድሎ የቀሩትን ወደ ባቢሎን ወስዷቸዋል። ይህ ለመጨረሻ ጊዜ የይሁዳ መንግሥት መንግሥት አልባ ሆኖ የቀረበት ጦርነት ነበረ።

በዚያን ጊዜም የንጉሥ ሴዴቅያስን ልጆች በፊቱ ከገደሉዋቸው በኋላ የእርሱንም ዓይኖች ጐልጉለው በማውጣት አሳውረውታል። ወድያውም ወደ ባቢሎን ከወሰዱት በኋላ በዚያ ሞቶአል፤ ኤር.51፡10-11። በዚህ ሁኔታ የአይሁድ መንግሥት ከጠፋ በኋላ ወድያውኑ የአሕዛብ ዘመን ጀመረ። በሉቃ.21፡24 ላይ እንደተጻፈ ይህ የአሕዛብ ዘመን በምድር የሚቆየው የአይሁዶች መንግሥት ከጠፋበት ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ በምድር ለመንገሥ ዳግመኛ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ያለውን ወቅት ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ከዚህ በኋላ ናቡከደነፆር ነቢዩ ሕዝቄል እንደተነበየው ጢሮስን ከበባት። ይሁን እንጂ ከተማዋን ለመያዝ

13 ዓመት ወሰዶበታል። በዚህም በ13 ዓመት ጊዜ ውስጥ የጢሮስ ነዋሪዎች ንብረታቸውን በሞላ ከከተማቸው 1 ኪሎ ሜትር ርቃ ወደምትገኝ ደሴት አሸሽተው ነበር። በዚህችም ደሴት ላይ አዲስ ከተማ ሠርተው ስለነበር ንብረታቸውን ወደዚያ ስላጋዙ ናቡከደነፆር ጢሮስን በያዛት ጊዜ ከተማዋ ባዶ ስለነበረች ምንም ሊያገኝባት አልቻለም ነበር። ያም ሆነ ይህ ናቡከደነፆር ጢሮስን ለመቅጣት እንደተላከና ግብፅም ለድካሙ ዋጋ ተደርጋ እንደተሰጠችው ሕዝቅኤል ጽፎአል፤ ሕዝ.29፡18-20።

ኤርምያስ ናቡከደነፆር ድንኳኑን በግብፅ እንደሚተክል ትንቢት ተናግሮአል። ባቢሎን እጅግ በጣም ሰፊና ቅጥሩም በጠላት የማይበገር ሕዝቡም እርቀ መሳፍርት የሌለው ስለሆነ በእግዚአብሔር ተአምር ካልሆነ በስተቀር ከተማውን የሚይዝና ሕዝቡን ሊማርክ የሚችል ሠራዊት አይኖርም፤ ኤር.43፡8-13፤ ሕዝ.30። እነሆ የከተማው አሠራርና ስፋት እንደሚከተለው ነው። ከተማው የሰፈረው 85 ኪሎ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ ሲሆን ዙሪያውን ጠንካራ በሆነ ግንብ ተገንብቶ መዝጊያዎቹ ከናስ ብረት የተሠሩ ነበሩ። የከተማውም ቅጥር መቶ ሜትር ከፍታና 24 ሜትር ስፋት ያለው ነበረ። ይህ በዚህ ላይ የተጠቀሰው የባቢሎን ከተማ ግንብ በፈረሰ ጊዜ ሰዎች የፍርስራሹን ድንጋይ ለ2 ሺህ ዓመት ያህል እያጋዙ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። በአሁኑ ጊዜ በጥንታዊቱ ባቢሎን ውስጥ ቆሞ የሚታይ ምንም ዓይነት የድንጋይ ግንብ የለም። በዚያን ጊዜ ከነበሩት ከንጉሡ ቤተ መንግሥቶች መካከል አንዱ በሦስት ረድፍ በተሠሩ የድንጋይ ቅጥሮች የተከበበ ነበረ። የቅጥሩም ከፍታ 72 ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን የቤተ መንግሥቱ ሕንፃ ጫፍ ከመሬት ወደ ላይ 126 ሜትር የሚረዝም ነበር። ጥላት ሲመጣ በከተማውም ቅጥር ላይ ለማጥቃትም ሆነ ለመከላከል ወታደሮች የሚጠቀሙባቸው ርዝመታቸው 126 ሜትር የሚሆን በግንብ የተሠሩ ቦታዎች ነበሩ። ከዕለታት አንድ ቀን ናቡከደነፆር በኩራት «ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን የሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችም?» ብሎ መናገሩን ሳይጨርስ ከሰማይ ድምጽ መጥቶ ገሰጸውና እግዚአብሔር መንግሥቱን ወሰደበት። ናቡከደነፆር ይህን በመናገሩ ዓለም ሁሉ እንደ እግዚአብሔር እንድታመልከው እንደፈለገ ያሳያል፤ ዳን.4፡30። እርሱም እግዚአብሔር መንግሥቱን ለፈለገው ለማንኛውም ሰው መስጠት እንደሚችል እስከሚያውቅ ድረስ ልቦናውን ስቶ ለ7 ዓመት እንደ አውሬ ሆነ። በኋላም ናቡከደነፆር ንስሐ ገብቶ እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ገዢ እንደሆነ ከመሰከረ በኋላ በቀድሞ ክብሩ ላይ አስቀምጦታል፤ ዳን.4።

እርሱም ከእንግዲህ ወዲህ እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ አምላክ፥ የሰማይና የምድር ጌታ መሆኑን ማመኑንና በእርሱ ግዛት የሚገኙ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ይህን ጌታ እንዲያውቁና እንዲያመልኩ አዋጅ አሳወጀ፤ ዳን.4፡34-37። ቀደም ሲል እግዚአብሔር ባቢሎንን ያስነሣው አይሁድ በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹ የመግረፍያ ጅራፍ እንዲሆኑዋቸው ብሎ ነበር። ይህን ያላወቁት ባቢሎናውያን ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን የጣለ መስሎአቸው ብዙ ሊያጉላሉዋቸውና እንደተፈረደበት ሰው ያሰቃዩአቸው ጀመር። በኋለኛው ቀን ግን እግዚአብሔር የሚባርኳችሁን እባርካለሁ የሚረግሙአችሁን እረግማለሁ የሚለውን ቃል ኪዳኑን አስቦ የባቢሎን ጥፋት እንደተቃረበ ተናገረ። ወዲያውም ብዙ ሳይቆይ ፍርዱን በባቢሎን ላይ አምጥቶ መንግሥትዋን እንደሚከተለው ከፋፈላት፤ ሕዝ.35፡3-6። የባቢሎን መንግሥት ከናቡከደነፆር በኋላ፦ 1. አዊል ማርዶክ፤ 2. ሴሪግላደር ናቡኒደስና ባልሻደር ነበሩ፤ 2ኛ ነገ.25፡27፤ ኤር.52፡1-7፤ ዳን.5። ከዚህ በኋላ ባቢሎናውያን ወንጌልን



ሰምተው ስለ እውነተኛው አምላክ ብዙ አውቀዋል። አይሁድም በከለዳውያን ምድር በሜሶጶታሚያ ያካባቢ ሁሉ ከተማን ከትመው በነፃነት መኖር ጀመሩ። ሕዝቅኤልም በሁለቱ ወንዞችና በባሕሩ አካባቢ ለሚኖሩት ባቢሎናውያን ትንቢት ተናገረ። የእግዚአብሔር ባሪያ ዳንኤል በባቢሎን ከፍተኛ ደረጃና ሥልጣን ነበረው። የአምላክ ጥበቃ ሲድራቅና ሚሳቅን እንዲሁም አብደናጐን የተጠነቀቀላቸው በዚሁ ምድር ነበረ። ንጉሥ ናቡከደነፆር የሲድራቅ የሚሳቅና የአብደናጐ አምላክ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ለሕዝቡ ሁሉ ያወጀው በዚሁ ነበረ። ከዚህም በቀር ናቡከደነፆር በትዕቢቱ ተዋርዶ ልቦናውን ከነሳው በኋላ ንስሐ በመግባቱ ወደ ክብሩ በተመለሰ ጊዜ እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ለዓለም ሁሉ ሕዝብ አስታውቋል፤ ዳን.4። በኋላም አይሁድ በባቢሎን ምርኮ ሥር እንዲገዙ እግዚአብሔር የደነገገው 70 ዓመት ሲያበቃ ቂሮስ የተባለው ንጉሥ ባቢሎንን ከቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ በምርኮ የመጡትን አይሁድ በነፃነት ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ፈቅዶላቸዋል፤ ኤር. 25፡11-12፤ ኢሳ.44፡23።

ብልጣሶር ታብዮ ካህናት በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚገለገሉበትን የውርቅና የብር ዋንጫ በኃጢአት ግብዣው ላይ ስላረከሰ እግዚአብሔር በራሱ አገልጋዮች እጅ እንዲሞት አድርጐታል፤ ዳን.5፤ ኢሳ.13፡14፤ 21፡1-10፤ ኤር.50፡51፤ ኢሳ.13፡6፤ 17፤ 19፡14፤ ኤር.50፡21፤ 31፤ 33-34፤ 51፡11፤ 30-31፤ 37፤ 45፤ መዝ.137፡8-9። ይህ ሁሉ ጥፋት ተጠራቅሞ እጅግ ለምና ባለፀጋ የነበረችው ባቢሎን ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ወድቃ ወናና ባድማ ተደርጋ ምድረ በዳ ሆና ቀርታለች።

ባቢሎናውያንም ሆኑ አይሁዶች በአሕዛብ ዘመን የራሳቸው የሆነ ግዛትና መንግሥት የላቸውም። የእነርሱ ግዛት ያበቃው በአሕዛብ መንግሥት መጀመሪያ ላይ ነበረ። በዳንኤል 2 ላይ የተጠቀሰው ቃል ባቢሎን በዓለም መንግሥት ስትመስል በዓለም መንግሥት መጨረሻ ላይ የተነሣው ነፃ አውጭው የኢዮአቄም መንግሥት ደግሞ ሊመጣ ባለው በክርስቶስ መንግሥት ተመስሎአል።

በምዕራፍ 10 እንደተወሳው ከ549-331 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሁለተኛው የዓለም መንግሥት በመሆን የተነሣው የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ነበረ። በዳንኤል ራዕይ በተመለከተው የምስል ደረት ላይ የታዩት ሁለት ክንዶች አንደኛው በፋርስ ሲመስል ሁለተኛው ደግሞ በሜዶን ይመስላል። እነዚህ ሁለት ኃያላን የመጀመሪያው ንጉሥ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ራሳቸውን ከሥልጣኑ ሥር በማስገዛት ቆይተው ከሁለቱም የላቀው አስከፊው የቂሮስ መንግሥት ብቅ ሲል አብረውት ተገለጡ፤ ዳን.10፡1። ይህ መንግሥት እውን ከመሆኑ ከ160 ዓመት በፊት እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይያስ በኩል በስሙ ጠርቶታል፤ ኢሳ.44፡28፤ 45፡1-6። ቂሮስ ከዳርዮስ በታች ሆኖ የመንግሥቱ ዋና ጄኔራል በመሆን ሕዝቡን ይመራ ነበር፤ ዳን.6፡1። ፋርስ በዳንኤል 7፡5 ላይ እንደ ድብ በመሰለ አውሬ ተመስሎአል። ፋርስ የያፌት ዘር ናቸው። በዚህ ላይ የምናየው የዓለም መንግሥት ከሴምና ከካም ዘር ወደ ያፌት ዘር መተላለፉን ነው። በአሁኑ ጊዜ ዓለምን አጠቃሎ በአንድ መንግሥት ሥር የሚገዛ የዓለም መንግሥት የለም። ቢሆንም በማጨረሻ ዘመን አንዱና ለዘለዓለም ከሴም ዘር የሆነውን ክርስቶስ ይገዛታል።

## የፋርስ አሸናፊነት

ሜዶንና ፋርስ አንድነት ከሆኑ በኋላ ኃይላቸውን አስተባብረው ሊድያን፥ ግብፅንና ባቢሎንን አሸንፈዋል። በዳንኤል ትንቢት ውስጥ በድብ የተመሰለው ፋርስ ያሸነፋቸው ወገኖች ተጠቅሰዋል፤ ዳን.8፡54። ሁለት ቀንዶች ባሉት ዳንግላ በግ የሚመሰለው ይኸው የሜዶንና የፋርስ ንጉሥ በሰሜን ሊድያን በምዕራብ ባቢሎንን በደቡብ ግብፅን ያሸንፋል። በመጀመሪያ የበቀለውና ትንሹ ቀንድ የመጀመሪያ ሥልጣን የነበረውን ሜዶንን ያመለክታል። ሁለተኛውና ታላቁ ቀንድ ደግሞ በንጉሥ ቂሮስ ይመራ የነበረው የፋርስ መንግሥት ነው። የፋርስ ሠራዊት ባቢሎንን ከቁጥጥሩ ሥር አድርጉ በያዛት ጊዜ ባቢሎንን ያስተዳድር የነበረው ንጉሥ ብልጣሶር ነበረ። ይህም ንጉሥ ከጠላት ጋር በመሰባጠር ባቢሎንን ባስያዙዋት በራሱ አሽከሮች ተገድሏል፤ ዳን.5። እንግዲህ የኢሳይያስ ትንቢት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተፈጽሞአል፤ ኢሳ.45፡1-6። ኤርምያስ እንደተናገረው እግዚአብሔር በኃጢአትዋ ምክንያት የባቢሎንን መንግሥት ጥሎ ለማዋረድ ሲል ቀደም አድርጎ የፋርስ መንግሥት ኃይሉን እንዲያጠናክርና ሠራዊቱን እንዲያበዛ ግዛቱን ከግሪክ እስከ ሕንድ ከዚያም ከሕንድ ውቅያኖስ በሰሜን በኩል እስከሚገኘው እስከ ካስፒያን ባሕር ድረስ አስፋፍቶታል።

## የአይሁዶች ወደ አገራቸው መመለስ

ዳንኤል አይሁዶች ከባቢሎን ወደ ፋርስ ግዛት በተወሰዱበት ወቅት ለንጉሥ ቂሮስ እግዚአብሔር በነብዩ በኤርምያስ በኩል ከ70 ዓመት በኋላ ከምርኮ ተለቀው ወደ ትውልድ አገራቸው እንደሚመለሱ መናገሩን አስታወቀው፤ ኤር.25፡8-14። ከዚህም በቀር ነቢዩ ኢሳይያስ ከምርኮው ዘመን 160 ዓመት ቀደም ሲል አይሁዶች የምርኮውን ዘመን ከጨረሱ በኋላ ቂሮስ በሚባል ንጉሥ ነፃነታቸውን አግኝተው ወደ ትውልድ አገራቸው እንደሚመለሱ አስታውቆ ነበር። ልክ እንደትንቢቱ ቃል ዘመኑ ሲፈጸም ንጉሥ ቂሮስ ወደ አገራቸው መመለስ የሚፈልጉ አይሁዶች ሁሉ መመለስ እንደሚችሉ አሳወጀ፤ ዕዝራ 1፡1-2፤ 2ኛ ዜና 36፡22-23።

ከዚህ በኋላ በ536 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አዲሱን የይሁዳ ትውልድ በአባቶቹ ባሕል አሰልጥኖ ለማሳደግ ከ50 ሺህ የማያንሱ አይሁዶች በንጉሡ አዋጅ ወደ ትውልድ አገራቸው ተመለሱ።

## በፋርስ አገር የተደረገ የወንጌል ምስክርነት

በቂሮስ ትዕዛዝ ወደ አገራቸው ከተመለሱት ጥቂት አይሁዶች በስተቀር አብዛኛዎቹ በዓለም ሁሉ ስለተሠራጩ በሄዱበት የእግዚአብሔርን ማንነት ይመስክሩ ነበር። ይሁን እንጂ ከእነርሱ መካከል አብዛኛዎቹ ይህን ምስክርነት ለመስጠት ፈቃደኞች አልነበሩም። ያም ሆኖ ይህ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል የሚመስክሩ ሰዎች አጥቶ አያውቅም ነበር፤ ዮሐ.14፡7። አይሁዶች ለ200 ዓመት ያህል የሃይማኖት ነፃነት ተሰጥቶአቸው በነበረበት ዘመን በፋርስ ንጉሥ ትዕዛዝ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ዓለም አንድ ዓይነት ብሔራዊ ቋንቋ



እንዲኖራትና የወንጌል ተልዕኮም በነፃነት በየስፍራው እንዲዳረስ የትም ቦታ መሄድ የሚቻልበትን የነፃ ጉዞ ፈቃድ ሰጥቶ ነበር።

## የፋርስ መንግሥት ፍጻሜ

የፋርስ መንግሥት በምስሉ ላይ በተመለከተው በናስ በተመሰለው የግሪክ መንግሥት ፈረሰ። በዳንኤል ራዕይ ውስጥ የግሪክ መንግሥት በአውራ ፍየል ተመስሎ ነበር፤ ዳን.7፡6፤ 8፡5።

የዕዝራ፥ የነህምያና የአስቴር መጻሕፍት ታሪክ የተፈጸመው በዚሁ ንጉሥ ዘመነ መንግሥት ነበረ። ከነቢያትም ውስጥ ሐጌ፥ ዘካሪያስና ሚልክያስ ትንቢት የተናገሩት በዚሁ ተመሳሳይ ዘመን ነበረ።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## የአይሁድ ወደ ከነዓን መመለስ

አይሁድ ወደ ከነዓን የመመለስ ታሪክ በዕዝራና በነህምያ መጻሕፍት በሚገባ ተዘርዝሮ ተገልጿል። የዚያን ዘመን ነቢያት ሐጌና ዘካርያስ ነበሩ። በተለይ የመጽሐፈ አስቴር ታሪክ የተፈጸመው በፋርስ መንግሥት ዘመን አይሁዶች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ትዕዛዝ በወጣበት ጊዜ አካባቢ ነበረ።

## የቂሮስ ትዕዛዝ

አይሁድ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር ተማርከው ወደ ባቢሎን ከተወሰዱ በኋላ በዚያ በምርኮኝነት 70 ዓመት ኖሩ። በኋላም ባቢሎን በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ድል ተደርጋ ከተወሰደች በኋላ ልክ በ70 ዓመታቸው መጨረሻ ላይ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ ነፃነታቸውን አግኝተው ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ትዕዛዝ አውጥቶአል፤ ኤር.25፡11-12፤ 29፡11። ቂሮስ ትዕዛዝ ካወጣ በኋላ በፈቃደኝነት ወደ አገራቸው የተመለሱት አይሁዶች ቁጥር 50 ሺህ የሚሆል ነበረ። ከእነዚህም መካከል አብዛኛዎቹ የይሁዳ የብንያምና የሌዊ ነገዶች ነበሩ። በአሦር ንጉሥ ከተማረኩት ከአሥሩ ነገዶች ውስጥም ወደ አገራቸው ለመመለስ ልባቸው የተነሳሱ ሁሉ ተመልሰዋል። እነዚህ ነገዶች በዘሩባቤልና በካህናት አለቃ በኢያሱ ተመርተው ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ በጠላት ፈራርሳ የነበረችውን የኢየሩሳሌምን ከተማ መልሰው መጠገን ጀመሩ። ከዚህ በኋላ ወደ አገራቸው የተመለሱት እስራኤላውያን ሁሉ በአንድነት አይሁድ ተብለው መጠራት ጀመሩ፤ ዕዝራ 1፡6።

አይሁድ ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ ከተማዋን መልሶ ለማሰራት 20 ዓመት ወስዶባቸዋል። ሆኖም አይሁድ መልሰው የሠሩት የኢየሩሳሌም ከተማ ቀድሞ ሰለሞን ከሠራው እጅግ ያንስ ነበር። ያም ሆኖ ይህ ከተማው መልሶ ከተሠራ በኋላ ቀድሞ በውበቱ

ያውቁት የነበሩ ሽማግሌዎች በትዝታ በለቅሶ ሀቅ ብለው ሲሞቱ ወጣቱ ትውልድ ደግሞ ያያት የቅድመ አያቶቻቸው ከተማ መልሶ ተሠርቶ በማየታቸው በደስታ እልልታውን ያስተጋቡት ጀመር። በዚያን ጊዜ የልቅሶውንና የደስታውን ድምፅ ለመለየት በጣም ያስቸግራል። ጥቂት ቆየት ብሎ የሕዝቡ ድምፅ ሲረጋጋ ሐጌና ዘካርያስ የዓለም ንጉሥ የሆነው መሢሃችን ክርስቶስ ከጥቂት ዘመናት በኋላ በዚህ ሥፍራ ስለሚያልፍ ያ ቤተ መቅደስ እንደሚቀደስ ትንቢት ተናገሩ፤ ሐጌ 2፡1-9፤ ዘካ.9፡9። የመጀመሪያዎቹ አይሁዶች ቤተ መቅደሱን ለመሥራት በተመለሱ በ78ኛው ዓመትና ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በ7ኛው ዓመት የሙሴን ሕግ በመጻፍ እጅግ ፈጣን በነበረው በዕዝራ ተመርተው እጅግ ብዙ እስራኤላያን ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል፤ ዕዝራ 7፡8። ንጉሥ አርጤክስስም ዕዝራ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሕዝቡን እግዚአብሔርን ማወቅን ከሙሴ መጽሐፍ እንዲያስተምራቸው የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ መልካም በሆነች መጠን የሚያስፈልገውን በመስጠት በ458 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ላከው። ዕዝራ የሙሴ ሕግ የተጻፈበትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጸሐፊ ነበር፤ ዕዝራ 7፡6። በዚያን ዘመን ከዕዝራ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት የእስራኤል ልጆች ቁጥር 7000 ያህል ነበረ፤ ዕዝራ 7፡10። ከዚህ በኋላ 13 ዓመት ቆይቶ አርጤክስስ ነህምያን የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንዲጠግን ፈቀደለት። በዚህን ጊዜ አርጤክስስ ከነገሠ 20 ዓመት ሆኖት ነበር። ነህምያም ቅጥሩን ለማደስ ወደ ኢየሩሳሌም የተላከው በ445 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር፤ ነህም. 2፡1-8። ነህምያ ቅጥሩን እየጠገነ ሳለ ጠላቶቹ ለ52 ቀናች ያህል ቢያስቸግሩትም አይሁዶች የመከላከያ መሣሪያቸውን ታጥቀው በተመሳሳይ ጊዜ ግንቡን እንዲጠግኑ በማድረግ በእግዚአብሔር ዕርዳታ የጥገናውን ተግባር ሠርቶ ለመጨረስ በቅቷል፤ ነህም.4።

እነሆ ሰባ ሱባኤው ከዚህ ይጀምራል። ከዚህ በኋላ ከሕዝብ አንድ አስረኛ የሚሆኑት በእጣ በኢየሩሳሌም እንዲኖሩ ሲደረግ የቀሩት በተለያዩ የእስራኤል ከተሞች መኖር ጀመሩ፤ ዳን. 9።

ከአይሁድ ወገን የሆኑትና የቀሩት የእስራኤል ልጆች በአካባቢያቸው ከሚገኙ የአሕዛብ ጐሳዎች ጋር በጋብቻ ተጣምረው ስለተዋለዱ የቀሩት ያልተከላለሱት አይሁዶች እንደራሳቸው ወገን አድርገው አይቀበሉዋቸውም ነበር። ስለዚህ ከቀሩት አይሁዶች ተገልለው ይኖሩ ነበር። እነዚህ ከአሕዛብ የተከለሱት አይሁዶች ጌታ ኢየሱስ በሥጋ በምድር በነበረበት ዘመን ሳምራውያን እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት ናቸው። የቀሩት አይሁዶች ይንቋቸውና ይጸየፏቸው ስለ ነበረ ከእነርሱ ጋር በምንም ዓይነት ነገር አይተባበሩዋቸውም ነበር፤ ነህም.11፡1-2።

## መጽሐፈ አስቴር

በአስቴር መጽሐፍ በምዕራፍ 1፡1 ላይ የተጠቀሰው አርጤክስስ በዕዝራ 7 ና በነህምያ 2 ላይ ከሚገኘው አርጤክስስ ጋር አንድ ነው። በአንደኛው ክፍል ውስጥ የተጠቀሰው አርጤክስስ የተባለው ስሙ ሥልጣኑንና ክብሩን የሚገልጥ ሲሆን በሌላው ክፍል የተጠቀሰው አርጤክስየስ ግን በታሪክ መጽሐፍ ከታወቀው ሴደ ሴኤርርድሰ ከተባለው ንጉሥ ስም ጋር አንድ ነው። ስለዚህ በዕዝራ 7 እና በነህምያ 2 እንዲሁም በአስቴር መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው አርጤክስስ የተባለው ስም የአንድ ተመሳሳይ ግለሰብ ስም እንደሆነ ከዚህ ቀጥለን በአጭሩ እንገልጻለን።



ነህምያ ከንጉሡ ከአርጤክስስ ፈቃድ ተቀብሎ የኢየሩሳሌምን ከተማ ለማደስ በሄደ ጊዜ ንግሥቲቱ ከንጉሡ አጠገብ ተቀምጣ እንደነበረ ተናግሮአል። ስለዚህ ንግሥቲቱ በነህምያ መሄድ ምንም ተቃውሞ አለማሳየትዋ ይህች ንግሥት የአይሁድን ደኅንነት የምትወደው ንግሥት አስቴር ትሆናለች ብለን እንገምታለን። ይህ ባይሆን ኖሮ ነህምያ ፈቃድ በጠየቀበት ወቅት ንግሥቲቱ ከንጉሡ ጋር እንደነበረች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልተጠቀሰም ነበር። ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስና ስለበሮችው መቃጠል በሰማ ጊዜ እጅግ አዝኖ በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት እንደወደቀ በነህምያ መጽሐፍ ውስጥ ተጥቅሶአል፤ ነህም.1፡1-4። ነህምያ እጅግ አዝኖ ያለቀሰው ከረጅም ዘመን በፊት ባቢሎናውያን አፍርሰዋት ስለነበረችው ኢየሩሳሌም አልነበረም፤ ምክንያቱም ከእርሱ ቀደም ሲል ከዘጠኝ ዓመት በፊት ወደ ባቢሎን የተማረኩት አይሁዶች ነፃነታቸውን አግኝተው ከተመለሱ በኋላ ከተማዋን እንዳደሱ ያውቅ ነበር። ከዚህም በቀር ነህምያ ይህን ወሬ ከማስማቱ ከ13 ዓመት በፊት ዕዝራ አዲሱን ትውልድ በቤተ መቅደሱ ውስጥ እግዚአብሔርን ማወቅ ሊያስተምር ሄዶ እንደነበረ ያውቃል።

ስለዚህ ነህምያ በዚህን ጊዜ ያለቀሰው ሐማ አይሁድን ለማጥፋት ባደረገው ክስ መሠረት በኢየሩሳሌም የሚገኙ ጥቂት አይሁዶች እንደተገደሉና ከተማዋም በእሳት እንደተቃጠለች ስለሰማ ነው። ሆኖም በእግዚአብሔር ቸርነት አስቴርን በመጠቀም የሐማን ሀሳብ ገልብጦ አይሁድ ነፃነታቸው ተጠብቆ እንደ ማንኛውም ሕዝብ በሰላም በምድር እንዲኖሩ ተደርጓል።

ከዚህም በቀር ነህምያ በወቅቱ በከተማው ላይ በደረሰው የመፍረስና የመቃጠል አደጋ ብቻ ሳይሆን ስለ አይሁድ ሕዝብ መጎሳቆል አልቅሶ ነበር። ልክ ከዚህ በኋላ ነው ነህምያ ከተማውን መልሶ ለመጠገን ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው።

## የኢየሩሳሌም ከተማ አሠራር ቅደም ተከተል

1. በመጀመሪያ በፋርሱ ቂሮስ ትዕዛዝ አይሁዶች ወደ አገራቸው ተመልሰው ቤተ መቅደሱን እንዲያድሱ አዋጅ ተነገረ። ከዚህ በኋላ በዘሩባቤል መሪነት 50 ሺህ የሚያህሉአይሁዶች ወደ አገራቸው ተመልሰው ቤተ መቅደሱን በ20 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሠርተው ጨርሰዋል።
2. ከዚህ በኋላ 78 ዓመት ቆይቶ ንጉሥ አርጤክስስ ካህኑ ዕዝራ 7 ሺህ የሚያህሉ አይሁዶች አስከትሎ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድና በዚያ እግዚአብሔርን ማወቅ እንዲያስተምራቸው፥ ከዚህም በላይ መሪያቸው ሆኖ እንዲያስተዳድራቸው ላከው።
3. እንደገና ሐማ አይሁድን በከሰሰበት ዘመን ንጉሡ ያወጣው ትዕዛዝ መልሶ ከመገልበጡ በፊት የኢየሩሳሌም ከተማ ፈርሶ በሮችዋ በእሳት ተቃጠሉ። በዚያን ዘመን ሸሽተው ካመለጡት ጥቂት አይሁዶች በቀር በኢየሩሳሌም ብዙዎቹ አይሁዶች ተገድለው ነበር።
4. ከ13 ዓመት በኋላ አይሁዳዊቷን አስቴርን ያገባው አርጤክስስ ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር መልሶ እንዲጠግን ፈቅዶ ያሰናብተዋል። ነህምያ ከተማዋን አድሶ ከተመለሰ በኋላ ይሁዳ እንደገና ከፋርስ ግዛት በታች እንድትሆን ተደርጋ ነበረ። ሆኖም ሙሉ በሙሉ በፋርስ መንግሥት እጅ አልገባችም ነበር።

## የአይሁድ ምኩራብ አመሠራረት

የአይሁድ ሙኩራቦች ሥነ ሥርዓት የተጀመረው በዕዝራና በነህምያ ዘመን ነበረ። ከዚያ በፊት ግን በአይሁድ አገር ምንም ዓይነት ምኩራብ አልነበረም።

እነዚህ ምኩራቦች ከተሠሩ በኋላ ዕዝራና ነህምያ ለአይሁዶች እግዚአብሔርን ማወቅና የሙሴን ሕግ በዚህ ስፍራ ያስተምሩአቸው ጀመር። በኋላም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ደቀ መዛሙርታቸውን ሕግና ሥርዓታቸውን ያስተምሩ የነበሩት በእነዚሁ ስፍራ ነበረ። ፈሪሳውያን የሙሴን ሕግ በመጠበቅ፥ በቅዳሴና በጾም እንዲሁም የተለያዩ ወጎችን በመጠበቅ የታወቁ ሲሆኑ ሰዱቃውያን ደግሞ የሙሴን ሕግ በመጠበቅ ከፈሪሳውያን የማይለዩ ቢሆኑም እንደ ፈሪሳውያን ስለ ሙታን ትንሣኤና ስለ ዘለዓለም ሕይወት አያምኑም ነበር።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለው ዘመን

የባቢሎን መንግሥት ለ70 ዓመት ከቆየ በኋላ በፋርስ መንግሥት ተይዞ ከፈረሰ በኋላ መንግሥት ተቋቋመ። ከዚያም በዳንኤል ምዕራፍ 8 ላይ እንደተወሳው የፋርስ መንግሥት ለ200 ዓመት ያህል ቆይቶ በግሪኮች እጅ ፈረሰ። እነዚህ መንግሥታት የተቋቋሙት በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል በነበረው ዘመን ውስጥ ነው። በኋላም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣበት ዘመን አካባቢ እንደገና በፋንታው የግሪክ መንግሥት ወድቆ የሮም መንግሥት በዓለም ላይ የበላይነትን ሥልጣን ያዘ። እነዚህ መንግሥታት ሁሉ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን እስራኤልና ይሁዳ ይኖሩባት የነበሩበትን የአይሁድ ምድር በመፈራረቅ ገዝተዋት ነበር።

የመጀመሪያው የግሪክ ንጉሥ ታላቁ እስክንድር ነበረ፤ ዳን.8፡21። እርሱም 13 ዓመት ከነገሠ በኋላ መንግሥቱ ለአራት ተከፈለ፤ እነርሱም፦ ሦርያ፥ ባቢሎን፥ ግብፅና ግሪክ ናቸው፤ ዳን.8፡8፤22።

የግሪክ መንግሥት በዓለም ላይ በሰለጠነበት ዘመን የግሪክ ቋንቋ የዓለም መነጋገሪያ ቋንቋ ስለነበረ መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ በግሪክ ቋንቋ ለአሕዛብ ሁሉ ሊሰበክ ችሎአል። ከዚያም በኋላ በዚሁ ዓይነት መልክ ሁሉም ሊሰማው እንዲችል አዲስ ኪዳንም የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነበረ። ስለዚህ በዚያን ዘመን እግዚአብሔር ግሪክ የዓለም መንግሥት እንዲሆን የፈቀደው ወንጌል ለዓለም ሁሉ እንዲዳረስ ሳይሆን አይቀርም።

ከዚህ መንግሥት በኋላ የተነሳው የሮም መንግሥት ነበረ። በመሠረቱ ይህ መንግሥት የእግዚአብሔር ጠላት ቢሆንም ከአገር ወደ አገር የሚወስዱ ብዙ የተመቻቹ መንገዶችን ስለዘረጋ ለወንጌል ስርጭት ታላቅ አገልግሎት ሰጥቶ ነበረ። ይህ ባይሆን ኖሮ የወንጌል ስርጭት በዚያን ዘመን በቀላሉ ዓለምን ባላዳረሰ ነበር።



## 3 ጽሑፍ

እግዚአብሔር አይሁዶችን ከአገራቸው ማርከው እንዲወስዷቸው ባቢሎናውያንን አስነሥቶባቸዋል። ይህ በመሆኑ የእግዚአብሔር ኃያልነት በናቡከነደፆር ፊት ስለታየ ቃሉ በድፍን የባቢሎን ግዛት በሞላ ለመሰበክ ችሎአል። የዓለም ሕዝብ የእግዚአብሔርን ኃያልነት አውቆአል። ስለዚህ አይሁድ ወደ ባቢሎን ባይማረኩ ኖሮ ቃሉ በዚህ መጠን በዓለም ዙሪያ ሊሠራጭ ባልቻለም ነበር። ከዚያም የፋርስ መንግሥት በተነሳበት ዘመን በሩቅና በቅርብ ያሉት የአሕዛብ መንግሥታት በአንዱ በግሪክ ቋንቋ ይጠቀሙ ስለ ነበረ ከበፊቱ በበለጠ መጠን ስለ እግዚአብሔር ያልሰሙ አረማውያን ሁሉ የቃሉ የምስራች በቀላሉ ሊደርሳቸው ችሎአል። በዚያን ዘመንም አዲስ ኪዳን በግሪክ ሲጻፍ ብሉይ ኪዳን ደግሞ ወደ ግሪክ እንዲተረጐም ተደርጓል።

ከዚህም በኋላ የፋርስ መንግሥት ወድቆ የሮም መንግሥት አጠቃላይ የዓለም አስተዳዳሪ በሆነበት ወቅት የሮም መንግሥት ያለ አንዳች ችግር ከአገር ወደ አገር ሊያስኬዱ የሚያስችሉ ታላላቅ አውራ መንገዶችን ዘረጋ። ይህ በመሆኑ እግዚአብሔር ወንጌልን በየስፍራው ለማዳረስ እንዲችል የመንገድ ችግር እንዳይኖር የሮምን መንግሥት አስነሥቶታል ማለት ይቻላል።

እነዚህ ሁሉ መንግሥታት ከእግዚአብሔር መንገድ የራቁና የቃሉ ጠላቶች ሆነው ሕዝቡን ያስጨንቁ የነበሩ ቢሆንም እግዚአብሔር የወንጌል መሠራጫ ምክንያት አድርጐ ተጠቅሞባቸዋል።

በአሁኑ ዘመን ግን ወንጌል እንደልብ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ሊሠራጭ ያልቻለበት ምክንያት በክርስቶስ ደኅንነትን ያገኙ የእግዚአብሔር ልጆች የቃሉን የምስራች ይዘው በየሥፍራ ሁሉ ለመሄድ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ነው።

ከቃሉ ብቻ ሳይሆን በታሪክም እግዚአብሔር ማንም ሰው ንስሐ ገብቶ እንዲድን እንጂ መጥፋቱን እንደማይፈልግ በሚገባ እንረዳለን። ስለዚህ ዳዊት በአሮጌው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም «የሰው ቁጣ ያመሰግንሃልና» ይላል፤ መዝ.76፡10። በታሪኩ እንደተማርነው የዓለም መንግሥታት ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ተቆጥተው ነበር። ሆኖም በቁጣቸው በኩል ለወንጌል መንገድ ይከፈት ነበር። እርሱም በዘመናት ሁሉ «ራሱን ያለ ምስክር አልተወም» የሐዋ.14፡17።